# የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል
# ቅዱስ ሉቃስ እንደ ጻፈው፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

# ክፍል - ሁለት

## ማውጫ


ጥናት 28፡ ደቀመዝሙርነት የሚያስከፍለው ዋጋ 2

ጥናት 29፡ መከሩ ብዙ ነው 3

ጥናት 31፡ የሚያስፈልገው ነገር 5

ጥናት 32፡ ፀሎት 6

ጥናት 33፡ ከጌታ ጋር ማከማቸት 7

ጥናት 34፡ የፃፎችና ፈሪሳዊያን ግብዝነት 7

ጥናት 35፡ ለደቀመዛሙርቱ የተሰጠ ምክር 8

ጥናት 36፡ አትጨነቁ 10

ጥናት 37፡ ነቅቶ መጠበቅ 11

ጥናት 38፡ ዘመንን መመርመር 12

ጥናት 39፡ የእግዚአብሔር መንግስት 13

ጥናት 40፡ የታላቁ እራት ግብዣ ጥሪ 14

ጥናት 41፡ የእግዚአብሔር አባትነት 15

ጥናት 42፡ የብልጉ መጋቢ ምሳሌነት 16

ጥናት 43፡ የባለጠጋውና የአልዐዛር ምሳሌ 17

ጥናት 44፡ ይቅርታ፣ እምነትና ምስጋና 18

ጥናት 45፡ የእግዚአብሔር መንግስት መምጣት 19

ጥናት 46፡ ሕፃናትና ባለ ጠጎች በእግዚአብሔር መንግስት 20

ጥናት 47፡ በርጠሜዎስና ዘኪዎስ 21

ጥናት 48፡ የአስሩ ምናምን ምሳሌ 22

ጥናት 49፡ ሆሳህና 23

ጥናት 50፡ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ የማዕዘን ራስ ሆነ 24

ጥናት 51፡ የዘመኑ መጨረሻ ምልክቶች 25

ጥናት 52፡ የመጨረሻው እራት 26

ጥናት 53፡ ኢየሱስ በጌቴሰማኒ 27

ጥናት 54፡ ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ 28

ጥናት 55፡ ጲላጦስና ሄሮድስ 29

ጥናት 56፡ የኢየሱስ ስቅለትና መሞት 30

ጥናት 57፡ የኢየሱስ መቀበርና ትንሳኤ 31

ጥናት 58፡ የኤማሁስ መንገደኞች 32

ጥናት 59፡ የኢየሱስ ሕያውነትና ዕርገት 33

# መግቢያ

በክፍል አንድ ጥናታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ ያለውን የክብሩን ስፍራ ትቶ የጠፋውን የሰውን ልጅ ሊፈልግ ወደ ምድር እንደመጣ፤ ከድንግል ማሪያም በመንፈስ ተፀንሶ እንደተወለደና በገሊላ አውራጃ በናዝሬት ከተማ እንደኖረ ተመልክተናል። ዕድሜውም 30 ዓመት ሲሞላ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥምቁ ዮሐንስ ሲጠመቅ ሳለ ሰማይ ተከፍቶ "የምወደህ ልጄ አንተ ነህ፣ በአንተ ደስ ይለኛል" የሚል ድምፅ ከሰማይ እንደመጣ ተመልክተናል። ኢየሱስ ክርስቶስ በገሊላ አውራጃ ውስጥ በተለያዩ ከተማዎች በመዘዋወር አገልግሏል፤ በሽተኞችን ፈውሷል፤ በአጋንንት እስራት የታሰሩትን ነፃ አውጥቷል፤ የዕውሮችን ዓይን አብርቷል፤ ለምፃሞችን አንፅቷል፣ ሙታንን አስነስቷል፤ ብዙ የተለያዩ ተዓምራቶችን አድርጓል፤ የመንግስቱን ወንጌል በስልጣንና በጥበብ ሰብኳል።

በዚህ ክፍል ሁለት ጥናታችን ደግሞ የኢየሱስን የኢየሩሳሌምን ጉዞ፤ የኢየሱስን መከራ፤ ስቅለት፤ ሞት፤ ትንሳኤና ዕርገቱን እንመለከታለን።

እግዚአብሔር አምላክ ጥናቱን ለሁላችን ይባርክልን።

# ጥናት 28

## *ደቀመዝሙርነት የሚያስከፍለው ዋጋ*

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 9:57-62፣ 14:25-35

***መግቢያ***

በዛሬው ጥናት ደቀመዝሙር መሆን ሊያስከፍል ስለሚችለው ዋጋ  ደቀመዛሙርት ለመሆን ወደ ኢየሱስ መጥተው ለነበር ሰዎች ኢየሱስ ከተናገረው እንመለከታለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ቁ. 57 - ወደምትሄድበት ሁሉ ልከተልህ ብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስ ምን መልስ ሰጠ? ከመልሱ ደቀመዝሙርነት ምን ዋጋ ያስከፍላል ትላለህ? ማቴ 8:19

2. ቁ. 59 - ኢየሱስ "ተከተለኝ" ያለው ሰው ምን መልስ ሰጠው? ይህ ሰው እንዳይከተለው ምክንያቱ ምን ነበር? ከዚህስ ደቀመዝሙር መሆን ምን ሌላ ዋጋ ያስከፍላል ትላለህ?

3. በቁ. 61 ላይ የተጠቀሰው ሰው ኢየሱስን ለመከተል ያቀረበው ቅድመ ሁኔታ  ምንድን ነው? ኢየሱስ በምሳሌ የመለሰውን አብራራ።

4. በም. 14:25-33 ያለውን በመዳሰስ ደቀመዝሙርነት ምን ማለት ነው ትላለህ? በክፍሉ መሠረት ደቀመዝሙር መሆን የሚያስከፍለውን ዋጋ በዝርዝር ተወያዩበት።  "መስቀሉን መሸከም" ማለት ምን ማለት ነው?

5. በቁ. 25-35 ባለው ክፍል ውስጥ ኢየሱስ ደቀመዝሙር መሆን  ምን ያህል ዋጋ እንደሚጠይቅ ለማብራራት የተጠቀበትን ሦስት ምሳሌዎች ተወያዩበት።

6. የጨው ጥቅም ምንድን ነው? ጨው የጨውነቱን ባህሪ ቢያጣ መጨረሻው ምን ይሆናል?

***የማዛመድ ጥያቄዎች***

7. ደቀመዝሙርነት ሊያስከፍል የሚችለውን ዋጋ በመረዳት የፅድቅ ሕይወትና አገልግሎት ከጌታ ብድራት እንዳለው በማመን በምን ያህል መሰጠት የክርስቶስን መስቀል ተሸከመህ በዕለት ተዕለት ሕይወትህ ጌታን ትከተላለህን?
8. ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ሰው ምን ዓይነት ሰው ነው? ከዛሬው ጥናት መጨረሻው ምን እንደሚሆን ተማርክ?
9. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

***ማጠቃለያ***

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ የመስቀል ስራ በማመን የዘላለም ሕይወትን በነፃ ተቀብለናል። ሆኖም ደቀመዝሙርነት ዋጋ የሚያስከፍል ሕይወት ነው። ብድራታቸውን ከሩቅ ተመልክተው፤ በዚህ ዓለም ያለውን መከራ ታግሰው፤ በጊዜያዊው ጥቅም ሳይታለሉ መንፈሳዊ ሩጫቸውን በትዕግስት የሚሮጡ የክብር ሽልማታቸውን በመጨረሻ  ፃድቅ ፈራጅ  ከሆነው ጌታ ይቀበላሉ።

***የቃል ጥናት***

"ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግስት የተገባ አይደለም"  ሉቃ 9:62

# ጥናት 29

## መከሩ ብዙ ነው

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 10፡1-24

### መግቢያ

ባለፈው ጥናት ደቀመዝሙርነት የሚያስከፍለውን ዋጋ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ኢየሱስ ሰባሁለት ሰዎችን የእርሱ አምባሳደር አድርጎ እንደሾማቸውና ወደሚሄድበት ከተማና ቦታ ሁሉ ቀድመው እንዲሄዱና እንዲያስተምሩ እንዴት እንደላካቸው እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቁ. 1 - ኢየሱስ ሰባሁለቱን አምባሳደሮች እንዴት አድርጎ ላካቸው? በዚህ መልክ ለመላክ መምረጡ ለምን የሚጠቅም ይመስልሃል?
2. በቁ.2 ላይ "መከሩ ብዙ ነው ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው" ሲል ምን ማለት ነው? ለዚህስ ምን አድርጉ ብሎ አዘዛቸው?
3. በቁ 3 "እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ" ሲል በጎች እነማን ናቸው? ተኩላዎቹስ? ይህ ስለሚሄዱበት ስፋራ ወይም ስለሚያገለግሉት አገልግሎት ምን ያሳያል?
4. በቁ 4 ላይ "ኮረጆም ከረጢትም ጫማም አትያዙ" ብሎ ጌታ ኢየሱስ ለምን ያዘዛቸው ይመስልሃል? ከጢሞ 2:4-6 ጋር በማዛመድ ተወያዩበት።
5. ኢየሱስ ሰባሁለቱ ወደሚሄዱበት ከተማና ቦታ ሁሉ ለሰዎች እንዲነግሩት የፈለገው ዋናው መልዕክት ምን ነበር? ተወያዩበት።
6. ሰባሁለቱ አምባሳደሮች ደስ እያላቸው ተመልሰው ጌታ ሆይ አጋንንት ሁሉ በስምህ ተገዙልን ሲሉት ምን መልስ ሰጣቸው? ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሀሴት ያደረገበትስ ምክንያት ምን ነበር?

### የማዛመድ ጥያቄዎች

7. ኢየሱስ በቁ. 16 ላይ "የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል" በማለት የእርሱ አንባሳደሮች እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል። የዚህን የአንባሳደርነትን ጥሪ በሙሉ በመረዳት ምን ያህል ለጥሪው የሚመጥንን ሕይወት እንኖራለን?
8. በዛሬው ጥናት መሠረት ሁሌም ደስ ልንሰኝበት የሚገባን ነገር ምንድ ነው? ይህስ ለእኛ የየዕለቱ ምን ያህል የደስታችን ምንጭ ሆኖልናል?
9. ዛሬም መከሩ ብዙ ሰራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው። የመከሩ ጌታ ለመከሩ ስራ እንዲልክህ ምን ያህል ትፀልያለህ?
10. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### ማጠቃለያ

በዘመናት መሀካል እራሱን ያለምስክር የማይተው የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር በዚህ ዘመን በምድር የእርሱ ተወካዮች እንድንሆን አምባሳደሮቹ አድርጎ ሾሞ አስቀምጦናል። የጥሪያችንን ትልቅነት በመረዳት ጥሪያችንን በሚመጥን ሕይወት ልንኖር ይገባላል።

### የቃል ጥናት

"መከሩስ ብዙ ነው፤ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ለመከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት" ሉቃ 10፡2

# ጥናት 30
# ደጉ ሳምራዊ

**የምንባብ ክፍል**፡ ሉቃ 10:25-37

## መግቢያ

ባለፈው ጥናት ኢየሱስ ሰባሁለት ሰዎችን የእርሱ መልዕክተኞች አድርጎ በመሸም ወደሚሄድበት ከተማና በታ ሁሉ ቀድመው እየሄዱ እንዲያስተምሩ እንደላካቸው ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናት አንድ የአይሁድ ህግ አዋቂ ሊፈትነው ፈልጎ “ባልንጀራዬ ማነው?” ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስ ስለደጉ ሳምራዊ በምሳሌ መልስ እንደሰጠው እንመለከታለን።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ. 25-28 አንድ የህግ አዋቂው ጌታ ኢየሱስን ቀርቦ “የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን ላድርግ?” ብሎ ሊፈትነው ለጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስ “በሕግ የተፃፈው ምንድን ነው እንዴትስ ታነበዋለህ ብሎ ጥያቄውን በጥያቄ ሲመልስ የሕግ አዋቂው ምላሽ ምን ነበር? ተወያዩበት።
2. የህግ አዋቂው “ባልንጀራዬ ማን ነው?” ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስ በሰጠው ምሳሌ ውስጥ ምን ተማርክ? በወንበዴዎች ተደብድቦ ለተጣለው ሰውዬ ካህኑና ሌዊው ከንፈር መጥጠው ቢያልፉም ሳምራዊ ሰው ግን ምህረትና ቸርነት ማድረጉ ስለ ሳምራዊው ሕይወትና ማንነት ምን ያሳየናል? ስለ ካህኑና ስለሌዊውስ?
3. ደጉ ሳምራዊ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀዬ፣ ሐይማኖት ሳይለይ በሕይወትና በሞት መካከል ለነበረው ሰው ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ ያደረገለትን ዘርዝር?
4. በቁ. 27 እና 37 ላይ “ሂድ አንተም እንዲህ አድርግ” ሲለው እንመለከታለን። የመታዘዝንና የማድረግ ሕይወት አስፈላጊነትን ተነጋገሩበት።
5. በቁ. 29-37 ኢየሱስ ለሕግ አዋቂው ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?

## የማዛመድ ጥያቄዎች

6. በክፍሉ መሠረት ባልንጀራ የምንለው ምን ዓይነትን ሰው ነው? ሰዎችን ሳንለይ የመዋደዳችን ልክ እስከምን ድረስ ነው?
7. ኢየሱስ በክፍሉ በተደጋጋሚ “ሂድ አንተም እንዲህ አድርግ” ብሎ ሲል ለሕይወት የሚሆነን መስማታችን ወይንም ማወቃችን ሳይሆን ያወቅነውን ማድረጋችን መሆኑን ትረዳለህን?
8. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

## ማጠቃለያ

የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ቃል በተደጋጋሚ በተለያየ ሁኔታ ሰምተናል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውና እኛን ለሕይወት የሚያበቃን የሰማነውን ቃል ማድረጋችን ወይንም በቃሉ መኖራችን ነው። በዛሬው ክፍል እንደተመለከትነው ቡዙ ጊዜ ቃሉን ከሰሙት ካህንና ሌዋዊ ይልቅ ሳምራዊው ሰው በወንበዴዎች ተደብድቦ ለተጣለው እንዳዘነለትና ምህረት እንዳደረገለት እኛም ባልንጀሮቻችንን እንደራሳችን አድርገን በመውደድ በጎ ነገርን ለሌሎች ልናደርግ ይገባናል።

## የቃል ጥናት

“ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ” ሉቃ 10:42

# ጥናት 31

# የሚያስፈልገው ነገር

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 10:38-42፤ 12:22-31

## መግቢያ

ባለፈው አንድ የአይሁድ ህግ አዋቂ ሊፈትነው ፈልጎ “ባልንጀራዬ ማነው?” ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ ኢየሱስ ስለደጉ ሳምራዊ በምሳሌ መልስ እንደሰጠው ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ኢየሱስ ሳንጨነቅና ሳንባክን የእግዚአብሔርን ፅድቅና መንግስት በቅድሚያ መፈለግ እንደሚገባን ያስተማረውን እንመለከታለን።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ 38-40 - የማርታንና የማርያምን አገልግሎት በማነፃፀር ተወያዩበት። እንዲህ አይነት ሕይወት ዛሬ በቤተክርስቲያን ወይንም በሕይወታችን ምን ያህል ይታያል ትላለህ?
2. በቁ 41-42 - ኢየሱስ የማርያምና የማርታን  አገልግሎት የተመለከተው  እንዴት ነበር? “የሚያስፈልገው አንድ ነገር ብቻ ነው” ብሎ አጥብቆ የተናገረበት ምክንያት ምንድን ነው? ተወያዩበት።
3. በቁ. 22 - ኢየሱስ አትጨነቁ ብሎ ሲያስተምር ከክፍሉ መጨነቅ ምን ማለት እንደሆነ ትረዳለህ? ስለ ወደፊት ማሰብና ማቀድን ከዚህ ሀሳብ ጋር እንዴት ታዛምደዋለህ? ፊል 4:6 ፤  1ጴጥ 5:7
4. በቁ. 23 - ለደቀመዛሙርቱ ሲናገር “ህይወት ከምግብ ሰውነትም ከልብስ ይበልጣል” ሲል ይህ ንፅፅር ለህይወት ቅድሚያ ከመስጠት አኳያ ምን መልዕክትን ያስተላልፋል? ማቴ 16:26
5. ከቁ 24-27 - እንስሳትና አበቦችን አስመልክቶ ኢየሱስ በሰጠው ምሳሌ ሊያስተምር የወደደው ሀሳብ ምንድን ነው?
6. ከቁ 29-31 - የእግዚአብሔርን መንግስትና ጽድቁን ከሌላው አስቀድመን መሻት ሊያስጨምርልን የሚችለው በረከት ምንድን ነው? ከራስህ የህይወት ተሞክሮ (ምስክርነት) ጋር በማዛመድ አስረዳ።

## የማዛመድ ጥያቄዎች

7. በዛሬው ጥናት መሰረት በሕይወታችን የሚያስፈልገው ጥቂት ወይንም አንድ ነገር ምንድን ነው? አንተስ በማርታ አገልግሎት እንደታየው አይነት መባከን በሕይወትህ ሳይነግስ ከጌታ እግር ስር በመሆን ቃሉን ለማድመጥ፣ ለማጥናት፣ ለመመስከር ጊዜህን ትሰዋለህን?
8. እንዳንጨነቅ የእግዚአብሔር ቃል ቢመክረንም በአንዳንድ ጉዳዮች ስንጨነቅ እንታያለን። ይህ ከምን የተነሳ የሚሆን ይመስልሃል?
9. በእግዚአብሔር ላይ ልባችን ማሳረፍ የምንችለው እንዴት ነው?
10. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

## ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ቃል ለምድራዊ ኑሮአችን ከመጠን በላይ መጨነቅ እንደማይገባን ይመክረናል። ሰው በመጨነቅ ብዛት ሊቀይረው የሚችለው አንዳንች ነገር የለም። የሰማይ አባታችን የሚያስፈልገንን የሚያውቅ ከመሆኑም በላይ የድካማችንን ፍሬ የሚባርክ አምላክ ነው። በመስጠቱ የማይጎድልበት ቸሩ እግዚአብሔር ከስጦታው ሁሉ አስቀድመን የሰጪውን የእርሱን ፊት እንድንፈልግ ይመክረናል።

## የቃል ጥናት

“ይልቁንስ የእግዚአብሔርን መንግስት ጽድቁንም ፈልጉ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል”  ሉቃ 12:31

# ጥናት 32

## ፀሎት

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 11፡1-13፤ 18:1-14

### መግቢያ

ባለፈው ጥናት ስለ ደጉ ሳምራዊ እንዲሁም ስለ ማርታና ማርያም ታሪክ ተመልክተን ኢየሱስ የሚያስፈልገው አንድ ነገር ነው ብሎ ያስተማረውን አይተናል። በዛሬው ጥናት ኢየሱስ ለደቀመዝሙሩ ያስተማረውን ፀሎት እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከደቀመዝሙሩ አንዱ ኢየሱስ ፀሎት እንዲያስተምራቸው ለመጠየቅ የተነሳሳው ከምን የተነሳ ነበር?
2. ከቁ. 2-4 ጌታ ኢየሱስ ባስተማረው ፀሎት ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን ሀሳብ በማብራራት ተወያዩበት። ጌታ ካስተማረው ፀሎት አንፃር ዛሬ ፀሎታችን ምን ይዘት ሊኖረው ይገባል ብለህ ታምናለህ? ተወያዩበት።
3. በም 11:5-13 እና በም 18:1-16 ላይ አብዝቶ ስለመፀለይና ሳይታክቱ ስለመጠየቅ ኢየሱስ ስለተናገራቸው ምሳሌዎች ተወያዩበት። የተሰጠው ምሳሌ ስለምንድን ነው?
4. ኢየሱስ በቁ. 10 ላይ "የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና የሚፈልግም ያገኛል መዝጊያውንም የሚያንኳኳ ይከፈትለታል" ብሎ ካስተማረው ምን ትረዳለህ? ይህ የፀለይነውን ሁሉ እንቀበላለን ወደሚል መደምደሚያ ያደርሰናልን?
5. በቁ. 5-8 በሰው ወዳጅነትና በእግዚአብሔር ወዳጅነት መካከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት፤ በቁ. 11-13 በሰው አባትነትና በእግዚአብሔር አባትነት መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት ተወያዩበት።
6. በቁ. 13 ላይ "የሰማዩ አባታችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥም" ሲል ምን ማለቱ ነው?

### የማዘመድ ጥያቄዎች

7. ከክፍሉ ስለፀሎት ምን ተማርክ? እግዚአብሔር አምላክ እውነተኛ አባት መሆኑን ተረድተህ ፀሎትህን እንደሚሰማና እንደሚመልስ በማመን ምን ያህል ትፀልያለህ?
8. ሳይታክቱ ዘወትር የመፀለይ አስፈላጊነትን ከክፍሉ ምን ተማርክ? የህይወት ምስክርነት ካለህ ለቡድኑ አካፍል።
9. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### ማጠቃለያ

በክርስቶስ የመስቀል ሥራ ልጆቹ ያደረገን እግዚአብሔር ድምፃችንን በየጊዜው ሊሰማና እንደፈቃዱ መልስ ሊሰጠን የታመነ አባት መሆኑን አውቀን በተሰጠን የልጅነት መንፈስ ሳናቋርጥ ዘወትር በፀሎት ፊቱ ልንቀርብ ይገባናል።

### የቃል ጥናት

"ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያውን አንኳኩ ይከፈትላችኋል።" ሉቃ 11:9

# ጥናት 33

# ከጌታ ጋር ማከማቸት

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 11፡14-36

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ጌታ ኢየሱስ ስለ ፀሎት ያስተማረውን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ጋኔን የያዘውን ዲዳ ሰው ነፃ ካወጣና ከፈወሰ በኋላ ከእርሱ ጋር እንዴት መኖርና መመላለስ እንዳለብን ያስተማረውን እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ኢየሱስ በአጋንንት ለተያዘው ሰው ምን አደረገለት? ከፈውሱ በኋላ ሰውዬው ምን ለውጥ አመጣ? የህዝቡስ ምላሽ ምን ነበር?
2. ህዝቡ ኢየሱስን "በአጋንንት አለቃ በብዔል ዜቡል አጋንንትን ያወጣል" ብለው ባሉት ጊዜ ኢየሱስ ምን ብሎ መለሰላቸው? ተነጋገሩበት።
3. በቁ. 23 ላይ "ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፤ ከእኔም ጋር የማይሰበስብ ይበትናል" ብሎ ሲል ሊያስተላልፍ የወደደው መልዕክት ምንድን ነው?
4. በቁ. 29 ላይ "ይህ ትውልድ ክፉ ነው፤ ታምራዊ ምልክት ይፈልጋል" ካለ በኋላ"ከዮናስ ምልክት በስተቀር ሌላ ምልክት አይሰጠውም" ይላል። ጌታ ኢየሱስ በዚህ ሊያስተምር የፈለገው ምንድን ነው?
5. በቁ. 31-32 የደቡቧ ንግስት  እንዲሁም  የነነዌ ሰዎችም በፍርድ ጊዜ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነስተው ይፈርዱበታል ብሎ የተናገረው ምን ለመግለፅ ፈልጎ ነው?
6. በቁ. 35 ላይ "ስለዚህ በውስጥህ ያለው ብርሃን ጨለማ እንዳይሆን ተጠንቀቅ" ይላል። በውስጥ ያለው ብርሃን ጨለማ የመሆኑ ጉዳት ምንድን ነው?

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

7. በውስጣችን ያለው ብርሃን ጨለማ እንዳይሆን ልንወስድ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች ተወያዩ።
8. ዛሬ አንተስ (ቺስ) ተዐምራዊ ምልክቱን ወይንስ ጌታ ራሱን በህይወትህ ትፈልጋለህ (ሽ)?
9. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

ኢየሱስ የጠላትን ኃይል ለማፍረስ የተገለጠ መሲህ ነው። ሰዎች ደግሞ እርሱን በማመንና በማወቅ የበረከትና የድል ሕይወት ሊኖሩ ይችላሉ። ከእርሱ ጋር አለመሆን ከጠላት ሥር መውደቅ ነው። ከእርሱ ጋር አለማከማቸት፤ ሰብስቦ መብተን ነው።

### *የቃል ጥናት*

"ከእኔ ጋር የማያከማች እርሱ ይበትናል፤ ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል"  ሉቃ 11:23

# ጥናት 34

## የፃፎችና ፈሪሳዊያን ግብዝነት

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 11:37-54

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ጌታ ኢየሲስ ጋኔን የያዘውን ዲዳ ሰውዬ ነፃ ካወጣና ከፈወሰው በኋላ ከእርሱ ጋር እንዴት መኖርና መመላለስ እንዳለብን ያስተማረውን ተመልከተናል። በዛሬው ጥናት ኢየሱስ በአንድ ፈሪሳዊ ቤት ተጋብዞ ያንን አጋጣሚ በመጠቀም ሲያስተምር እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በክፍሉ ውስጥ ኢየሱስን በቤቱ የጋበዘው ሰው ምን ዓይነት ሰው ነበር?

2. ፈሪሳዊውን ያስደነቀው ነገር ምን ነበር? ኢየሱስ በልቡ ያለውን ሃሳብ አውቆ ምን ብሎ ተናነገራቸው? ከቁ 39-41 መሠረት የፈሪሳዊያን ችግር ምንድን ነበር?

3. ጌታ ኢየሱስ በቁ.41 "በውስጥ ያለውን ምጽዋት አድርጋችሁ ስጡ እነሆም ሁሉ ንጽህ ይሆናል" በማለት ሊይስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምንድን ነበር? ተወያዩበት።

4. በቁ. 42 የፈሪሳዊያን መሠረታዊ ችግር ወይንም ማድረግ ሲገባቸው ያላደረጉት ምንድን ነው? ይህ ምን ያህል አስፈላጊ ነው ትላለህ? ተወያዩበት።

5. በቁ.43 መሠረት የፈሪሳዊያን ችግር ምንድን ነው? በቁ. 44 "ሰዎች ሳያውቁ በላዩ የሚሄዱበት የተሰወረ መቃብር" ሲል ምን ማለቱ ነው?

6. ከ45-52 የህግ አዋቂዎች ችግር ምንድን ነበር? ኢየሱስ ምን ብሎ አላቸው? የእነዚህን አዋቂዎች ሕይወትና አገልግሎት ከሉቃ 17:2 ጋር በማዛምድ ተወያዩበት።

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

7. ቅድስናና ለእግዚአብሔር የመኖር ሕይወት ከውስጥ - ወደ - ውጭ መፍሰስ ያለበት መሆኑን ከክፍሉ ምን ያህል አስተዋልክ? ተወያዩበት።
8. ግብዝነት ምን ያህል አደገኛና ሕይወትን ሌላው ሳያውቅ ባዶ ሊያስቀር እንደሚችል ምን ያህል ተረዳህ?
9. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

እግዚአብሔር አምላክ የልብ አምላክ ነው። በነብዩ ኢሳያስ "ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባል፤ በከንፈሮቹም ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው" ይላል። (ኢሳ 29:13) ከፈሪሳዊያን እርሾ (ግብዝነት) ሁሌም ልንጠበቅ ይገባናል። እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሁታን ግን ፀጋን ይሰጣል።

### *የቃል ጥናት*

"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሁታን ግን ፀጋን ይሰጣል።" ያዕ 4:6

# ጥናት 35

## ለደቀመዛሙርቱ የተሰጠ ምክር

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 12:1-12

### መግቢያ

ባለፈው ጥናት ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት ተገኝቶ ስለ ግብዝነታቸው ሲነቅፋቸውና ሲመክራቸው ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠውን ምክር እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ በክፍሉ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምን የሚል ነው?
2. የእርሾ ባህሪው ምንድ ነው? በባለፈው ጥናታችን መሠረት የፈሪሳዊያን ሕይወት ምን ዓይነት ነበር?
3. በቁ. 2-3 ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ምን ብሎ አስተማራቸው? ደቀመዛሙርቱ እንዲኖራቸው የፈለገው ሕይወት ምን ዓይነት ነበር?
4. ከቁ 4-7 ትክክለኛና ትክክለኛ ስላልሆነ ፍርሃት ኢየሱስ ምን ብሎ አስተማረ? ትክክለኛ ያልሆነው ፍርሃት የሚመነጨው ከምንድ ነው? እግዚአብሔርን መፍራት ያለብን ለምንድን ነው?
5. በቁ.8 መሠረት በሰው ፊት የመመስከር ውጤቱ ምንድን ነው? በሰው ፊት እግዚአብሔርን መካድስ የሚያመጣው ጉዳት ምንድን ነው? መንፈስ ቅዱስን መሳደብ ማለት ምን ማለት ነው? የሚያስከትለውስ ጉዳት ምንድን ነው?
6. በቁ. 11-12 ላይ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የመንፈስ ቅዱስ ድጋፍና እርዳት እንደሚያገኙ ቃል የገባላቸው በምን ዓይነት ሁኔታ ሲያልፉ ነው?

### የማዛመድ ጥያቄዎች

7. ዛሬም አንተ የመንፈስ ቅዱስን እርዳታ በአገልግሎት ውስጥ ተለማምደኸው ታውቃለህ? የሕይወት ምስክርነት ካለህ ለቡድኑ አካፍል።
8. ዛሬስ አንተ(ቺ) የምትፈራው ነገር አለ? ከዛሬ ጥናት ምን ተማርክ(ሽ)?

### ማጠቃለያ

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ "አትፍሩ" የሚለው ቃል በብዛት የተጻፈና የተነገረ ቃል ነው። ሰውን፣ በምድር ያለውንና የሚሆነውን እንዳንፈራ በተደጋጋሚ ታዘናል። ይልቁንም የሰማይና የምድርን ፈጣሪ፣ ብቻውን አምላክና ጌታ የሆነውን እንድንፈራና በድፍረትም በሰው ሁሉ ፊት ስለ እርሱ እየመሰከርን እንድናገለግለው ታዘናል።

### የቃል ጥናት

"በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ ሁሉ፤ የሰው ልጅ ደግሞ በእግዚአብሔር መላእክ ፊት ይመሰክርለታል" ሉቃ 12:8

# ጥናት 36

## አትጨነቁ

**የምንባብ ክፍል፥** ሉቃ 12:22-31

***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠውን ምክር ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ኢየሱስ ስለምድራዊ ህይወታችን እንዳንጨነቅ ያስተማረውን ትምህርት እንመለከታለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በቁ. 22 ኢየሱስ አትጨነቁ ብሎ ሲያስተምር ከክፍሉ መጨነቅ ምን ማለት እንደሆነ ትረዳለህ? ስለ ወደፊት ማሰብና ማቀድን ከዚህ ሀሳብ ጋር እንዴት ታዛምደዋለህ? ፊል 4:6 1ጴጥ 5:7

2. በቁ. 23 ለደቀመዛሙርቱ ሲናገር "ህይወት ከምግብ ሰውነትም ከልብስ ይበልጣል" ሲል ይህ ንፅፅር ለህይወት ቅድሚያ ከመስጠት አኳያ ምን መልዕክትን ያስተላልፋል? ማቴ 16:26

3. ከቁ 24-27 እንስሳትና አበቦችን አስመልክቶ ኢየሱስ በሰጠው ምሳሌ ሊያስተምር የወደደው ሀሳብ ምንድን ነው?

4. ከቁ 29-31 የእግዚአብሔርን መንግስትና ጽድቁን ከሌላው አስቀድመን መሻት ሊያስጨምርልን የሚችለው በረከት ምንድን ነው? ከራስህ የህይወት ተሞክሮ (ምስክርነት) ጋር በማዛመድ አስረዳ።

***የማዛመድ ጥያቄዎች***

5. እንዳንጨነቅ የእግዚአብሔር ቃል ቢመክረንም በአንዳንድ ጉዳዮች ስንጨነቅ እንታያለን። ይህ ከምን የተነሳ የሚሆን ይመስልሃል?
6. በህይወታችን ለሚያጋጥመን ማንኛውም ጉዳይ ቅድሚያ የምንሰጠው እንዴት ነው? ከውሳኔያችንስ በኋላ አንዳንዴ ስለምን ልባችን የሚወላውል ይመስልሃል?
7. በእግዚአብሔር ላይ ልባችን ማሳረፍ የምንችለው እንዴት ነው?
8. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

***ማጠቃለያ***

የእግዚአብሔር ቃል ለምድራዊ ኑሮአችን ከመጠን በላይ መጨነቅ እንደማይገባን ይመክረናል። ሰው በመጨነቅ ብዛት ሊቀይረው የሚችለው አንዳንች ነገር የለም። የሰማይ አባታችን የሚያስፈልገንን የሚያውቅ ከመሆኑም በላይ የድካማችንን ፍሬ የሚባርክ አምላክ ነው። በመስጠቱ የማይጎድልበት ቸሩ እግዚአብሔር ከስጦታው ሁሉ አስቀድመን የሰጪውን የእርሱን ፊት እንድንፈልግ ይመክረናል።

***የቃል ጥናት***

"ይልቁንስ የእግዚአብሔርን መንግስት ጽድቁንም ፈልጉ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል" ሉቃ 12:31

# ጥናት 37

## ነቅቶ መጠበቅ

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 12:32-48

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ስለምድራዊ ህይወታችን እንዳንጨነቅ ኢየሱስ ያስተማረውን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት በትጋት ነቅቶ ስለመጠባበቅ እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ከቁ. 34 "ሰው የንብረቱ መዝገብ ባለበት ልቡም ደግሞ በዛ ይሆናል።" ሲል ምን ማለቱ ነው? ከቁ. 32-34 ባለው ክፍል ኢየሱስ ሊያስተምር የወደደው ሀሳብ ምን እንደሆነ አብራራ።

2. በቁ. 35 ላይ ጌታ ኢየሱስ የሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው? "ወገባችሁ የታጠቀ" ሲል ምን ማለቱ ነው?

3. ከቁ. 35-38 ኢየሱስ በየትኛውም የውድቅት ሌሊት አሳዳሪያቸውን ስለሚጠባበቁ አገልጋዮች በምሳሌ ተናገረ።

   ሀ. "ከሌሊቱም በሁለተኛው ወይንም በሦስተኛው ክፍል መጥቶ እንዲሁ ቢያገኛቸው" ሲል ይህ ምን ዓይነት ጊዜን ያመላክታል?
   ለ. ከቁ. 36-38 መሠረት ጌታው ሲተጉ ለሚያገኛቸው ምን ያደርግላቸዋል?
   ሐ. በምሳሌው ውስጥ ምን መልዕክት ለማስተላለፍ የፈለገ ይመስልሃል? ቁ.40

4. ከቁ. 42-46 በክፍሉ እንዳየነው በንቃት ተግቶ ለሚጠብቀው አገልጋይና ዝንጉ ሆኖ ለቆየው አገልጋይ አሳዳሪያቸው ወሮታውን እንዴት ይከፍላቸዋል? ከዚህ ምን እንማራለን።

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

5. ባላደራነት ተሰምቶን በጌታ ስራ ላይ ታማኝና ልባም ሆነን እንድንገኝ ምን ማድረግ አለብን?
6. ብዙ ከተሰጠው ሁሉ ብዙ የሚጠበቅ ከሆነ ከተደረገልን ምህረትና ቸርነት ጋር ሲተያይ ትጋታችን ምን ያህል ውለታ አሳቢ ነው ትላለህ?
7. ጌታ ባልጠበቅንበት ቀን ባላወቅንበትም ሰዓት ዳግም በክብር እንደሚመጣ አውቀን ምን ያህል ነቅተን እንጠብቀዋለን?
8. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

ለወደድነው ማንኛውም ነገር ልባችንን እንሰጣለን። በአንፃሩም ለእግዚአብሔር ባለን ፍቅር መጠን ከጊዜያችን ጀምረን ኑሮአችንን፣ ህይወታችንን እንሰጠዋለን። የተጠራነው ለአለም ብርሃን፣ ለምድርም ጨው እንድንሆን በመሆኑ የተጠራንበትን እንድንፈፅም በቃልና በሥራ እንደታማኝ ወታደር ዘወትር ዝግጁ ልንሆን ይጠበቅብናል። ጌታችን በክብር ሲገለጥ ወይም ወደ እኛ ሲመለከት ባዶ እጃችንን እንዳንታይ የተሰጠንን አደራ በትጋት እናከናውን። በብዙ ተጎብኝተን ብዙ ተቀብለናልና እንደተደረገልን መጠን ታማኞች እንሁን።

### የቃል ጥናት

"ጌታቸው በመጣ ጊዜ ሲተጉ የሚያገኛቸው እነዚያ ባሪያዎች ብፁአን ናቸው" ሉቃ 12:37

# ጥናት 38

## *ዘመንን መመርመር*

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 12:49-59

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ነቅተን፣ ወገባችንን ታጥቀንና መብራታችንን አብርተን ስለመጠባበቅ ተመለከተናል። በዛሬው ጥናት ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመናችን የተነሳ ሊያጋጥመን ስለሚችለው ተግዳሮትና ዘመንን ስለመመርመር እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በቁ. 49 ላይ "በምድር ላይ እሳትን ልጥል መጣሁ" ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. በቁ. 50 "የምጠመቃት ጥምቀት አለችኝ እስከትፈፀምም ድረስ እንዴት እጨነቃለሁ?" ብሎ ኢየሱስ ሲናገር ምን ለመግለጽ ፈልጎ ነው?
3. ከቁ. 51-53 ኢየሱስ "ሰላምን ለማስፈን የመጣሁ እንዳይመስላችሁ" ብሎ የተናገረበት ምክንያት አስረዳ። ይህንን ሀሳብ በዮሐ 14:27 ካለው ጋር በማነፃፀር ተነጋገሩበት።
4. ከቁ 54-56 ህዝቡ ዘመኑን መመርመር እንደሚችሉ ለማሳሰብ ኢየሱስ የተጠቀመባቸው ምሳሌዎች ምንድን ናቸው? ዘመንን መመርመር ማለት ምን ማለት ነው? ከምሳሌዎቹ ምን እንደተማርክ አብራራ።
5. ከባለጋራህ ጋር ወደ ዳኛ ፊት ከመቅረብህ በፊት ከቁ. 57-59 ያለው የምንባብ ክፍል በመመልከት
    - ሀ. ምን እንድታደርግ ተመክረሃል?
    - ለ. በራስህ አነሳሽነት ከሰዎች ጋር ተቻችሎ ስለመኖር ከዚህ ክፍል ምን ትማራለህ? ዕብ 12:14፤ ኤፌ 4:32

### *የማዘመድ ጥያቄዎች*

6. በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ ባለህ እምነትና የእግዚአብሔርን ቃል በመምረጥህ የተነሳ የቅርብና የሩቅ ዘመድ ወዳጆችህ ቢለዩህ ወይንም ገሸሽ ቢያደርጉህ ምን ማድረግ ይኖርብኛል ብለህ ታምናለህ? ሮሜ 12:14-21
7. ከሚመጣው ክፉ ነገር ሁሉ እንድንጠበቅ ዘመኑን በጥንቃቄ ልንመረምር ታዘናል። ታዲያ ይህ ያለንበትን ዘመን ከትንቢት ቃል (ከእግዚአብሔር ቃል) አይታ እንዴት ትመለከተዋለህ? 2ቆላ 4:5-6
8. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

የክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝነትን በመቀበላችን የተነሳ ከቅርብ ዘመዶቻችንና ጓደኞቻችን የመለየት ዕጣ ሊያጋጥመን ይችላል። ሆኖም በክርስቶስ ፍቅር ልንሸከመውና ብድራታችንን ተመልክተን ወደፊት ልንራመድ ይገባል። (ሮሜ 12:9 ማቴ 5:44) ይልቁንም ያለንበት ይህ ጊዜ ዘመነ ዕላቂ መሆኑን አውቀን በትንቢት የተፃፈው ሁሉ ይፈፀም ዘንድ ግድ በመሆኑ ነቅተን በትጋት ሩጫችንን ልንጨርስ ይገባናል።

### *የቃል ጥናት*

" . . . የምድሩንና የሰማዩን መልክ ልትመረምሩ ታውቃላችሁ፤ ነገር ግን ይህን ዘመን የማትመረምሩ እንዴት ነው?" ሉቃ 12:56

# ጥናት 39

## የእግዚአብሔር መንግስት

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 13:18-30

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ክርስቶስ ኢየሱስ በማመናችን የተነሳ ሊያጋጥመን ስለሚችለው መለያየትና ዘመንን ስለመመርመር ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ኢየሱስ ስለእግዚአብሔር መንግስት እንዲሁም በጠባቧ በር ስለመግባት ያስተማረውን እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ከቁ. 18-21 ኢየሱስ የእግዚአብሔር መንግስት ምን ትመስላለች ብሎ የገለፀባቸው ምሳሌዎችና የምሳሌዎቹ ፍሬ ሃሳቦች ምንድን ናቸው? ተወያዩበት። ማቴ 13:32

2. በቁ. 23-24 "በጠባቧ በር ለመግባት ተጋደሉ" እያለ ሲያስተምራቸው የነበረው መልዕክት ምንድን ነው? ከዚህስ ምን ትማራለህ? ማቴ 7:13-14

3. ከቁ. 25-28 ኢየሱስ አላውቃችሁም ከእኔ ራቁ የሚላቸው ሰዎች ህይወት ምን ዓይነት ነው ብለህ ታስባለህ?

4. በቁ. 29 ከእግዚአብሔር መንግስት ጎድለው በውጭ ጥርሳቸውን እያፏጩ የሚቀሩት ከምን የተነሳ እንደሆነ ግለጽ።

5. በቁ. 30 ኢየሱስ "ከኋለኞች ፊተኞች የሚሆኑ አሉ ከፊተኞቹም ኋለኞች የሚሆኑ አሉ" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አብራራ። ማቴ 20:1-16

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

6. የእግዚአብሔር መንግስት እንደሚስፋፋ በሰናፍጭ ዘርና በእርሾ ተመስሎአል። ታዲያ እኛ የመንግስቱ አምባሳደሮች የሆንን ክርስቲያኖች ምን የስራ ድርሻ እንዳለን ታምናለህ?
7. ከእግዚአብሔር መንግስት ወደኋላ እንዳንቀር ወይንም እንዳንመለስ ምን ዓይነት ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይኖርብናል ትላለህ?
8. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

አንተ ታንሽ መንጋ መንግስትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና አትፍሩ (ሉቃ 12:32) እንደሚል እግዚአብሔር አብ በክርስቶስ የመስቀል ሥራ ከጨለማው መንግስት ወደ ልጁ የፍቅሩ መንግስት በሚያስደንቅ አጠራሩ አምጥቶናል። በዚህ አዲስ መንግስት ውስጥ ንጉሱ ጌታችን ኢየሱስ ሲሆን እኛም ክርስቲያኖች የንጉሱ ካህናቶች ነን (1ጴጥ 2:9)። ይሁን እንጂ እንደመንግስቱ እውተኛና ታማኝ ዜጎች ተገቢውን ሕይወት በመኖር በጠባቧ መንገድ ላይ ፈቃዱን እየፈፀምን በጥንቃቄ ልንመላለስ ይገባል።

### የቃል ጥናት

"በጠባቧ በር ለመግባት ተጋደሉ፤ እላችኋለሁና ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ አይችሉምም" ሉቃ 13:24

# ጥናት 40

## የታላቁ እራት ግብዣ ጥሪ

**የምንባብ ክፍል፡** *ሉቃ* 14፡15-24

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ጌታ ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግስትና ስለ ጠባቧ በር የተናገረውን ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ደግሞ ስለ ዘላለም ሕይወት የግብዣ ጥሪ ኢየሱስ በምሳሌ ያስተማረውን እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ከቁ. 16-20 ባለው ክፍል ውስጥ ስለታላቁ እራት ግብዣ የሰሰጠውን ምሳሌ ተወያዩበት።
    *ሀ. እነማን ተጋበዙ? ስለ ጋባዡ ማንነት ተነጋገሩ።*
    *ለ. ታዳሚዎቹን ለመጥራት የተላከው ማን ነበር?*
    *ሐ. የታዳሚዎቹ (የተጋባዦቹ) ምላሽ ምን ነበር?*
    *መ. ይህ ጥሪ ምሳሌነቱ ምንድን ነው?*

2. የታጋባዡን ምላሽ በሰማ ጊዜ የጌታው ምላሽ ምንድን ነበረ? ለምን? ባሪያውን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?

3. በሁለተኛው ጊዜ ጥሪ የተጠሩት እነማን ነበሩ? ምላሻቸው ምን ነበር?

4. በቁ. 27 "ግድ በላቸው" ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህ ምናልባት የመጨረሻ ጥሪ መሆኑንና ለሌላ ጥሪ ጊዜ እንደሌለ ያሳያል ብለህ ትገምታለህ? ተወያዩበት።

5. የመጀመሪያዎቹ ታዳሚዎች ምላሽ ስትመለከት፣ ምላሹ በራሱ ነው ጌታውን ያስቆጣው ወይስ ከግብዣው ይልቅ የራሳቸውን ጉዳይ ማስቀደማቸው? በዛሬው የሕይወት መርሕ ይህን እንዴት ታየዋለህ?

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

6. በዛሬው ጥናት በኋለኛው ጥሪ መግባት የሆነልን የመንግስቱ ታዳሚዎች እንደሆንን ምን ያህል አስተዋልክ? ይህንን ታላቅ ጥሪ የሞትን ዋጋ ከፍሎ ወደ እኛ ይዞ የመጣልንን ጌታን ኢየሱስ ስታይ ለርሱ ያለህ አምልኮ፣ መታዘዝና መሰጠት ምን ያህል ነው?
7. ጌታው ለባሪያው "ግድ በላቸው" ባለው መሠረት ዛሬ ያለሙኑ ቤተሰቦችን፣ ባልንጀሮቻችንና እንዲሁም ሌሎችን ወደዚህ ታላቅ የእራት ግብዣ (የመጨረሻው ጥሪ) እንዲመጡ ምን ያህል ግድ ትላቸዋለህ?
8. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

*ወደ ገዛ ወገኖቹ ለማዳን መጥቶ የነበረው ጌታ እነርሱ ባለመቀበላቸው ምክንያት መዳን ለአሕዛብ (ለእኛ) ሁሉ ሆነ። ይህንን የተቀበልነውን የዘላለም ሕይወት ለሌሎች የማካፈል ግዴታ አለብን። ሳንታክት ዘወትር በፀሎትና ወጥቶ ለሌሎች በመመስከር ብዙዎችን ወደ መንግስቱ (ታላቁ ግብዣ) ልንጠራቸው ይገባል። የዚህ ታላቅ ግብዣ ተካፋይ እንዲሆኑ በፍቅር ግድም ልንላቸው ይገባል።*

### *የቃል ጥናት*

*"ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ ደቀመዛሙሬ ሊሆን አይችልም" ሉቃ* 11:26

# ጥናት 41

## የእግዚአብሔር አባትነት

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 15፡1-32

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ኢየሱስ ስለታላቁ ግብዣ ጥሪ በምሳሌ ያስተማረውን ተመልክተን ነበር። እኛም እንደ አማኝ ሌሎችን (በውጭ ያሉትን) ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲመጡ በፍቅር ግድ ማለት እንዳለብን አይተናል። በዛሬ ጥናት ደግሞ የጠፋውን ፍለጋ ከሰማይ የመጣውን ጌታ በምሳሌ እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ኢየሱስ የጠፋውን በግ ምሳሌ እንዲናገር ያነሳሳው ምንድን ነበር? የማንን ተቃውሞ በመመለስ ይመስልሃል?
2. ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ አንዱን ፍለጋ የሚሄድ እረኛ ምን ዓይነት ነው? ባገኘው ጊዜ ምን አደረገ? ይህ ስለ እግዚአብሔር ምን ያስረዳል? (ቁ. 6) ሐጢአተኛውንና የጠፋውን በግ እንዴት ታመሳስለዋለህ?
3. ከአስሩ አንድ ሳንቲም (ዲናር) የጠፋባት ሴት ምን አደረገች? ባገኘችውስ ጊዜ ምን አደረገች? ስለዚህች ሴት ባህሪ ምን ትረዳለህ?
4. ታናሹ ልጅ በቁ. 11-12 ላይ የሚደርሰውን ድርሻ ተቀብሎ ለመሄድ ምን ያነሳሳው ይመስልሃል? የአባቱ ምላሽ ምን ነበር?
5. የአባቱን ቤት ትቶ ከሄደ በኋላ ምን ሆነ? ወደ አባቱ ቤት ለመመለስ ምን አስገደደው? ይህንን ታላቅ ውሳኔ ስትመለከት እንዲወስን የረዳው ምንድን ነበር ትላለህ? ሲመለስ በምን ዓይነት ልብ ነበር?
6. የልጁን መመለስ በናፍቆት ይጠባበቅ ስለነበረው ስለዚህ አባት ባህሪ ምን ታያለህ? ባገኘው ጊዜ ምን አደረገ? ለልጁ ያለውን ፍቅርና ይቅርታ በምን መንገድ ገለፀው?
7. ታላቁ ልጅ የአባቱን ድርጊት ያልተረዳውና ያልተቀበለው ለምን ይመስልሃል? ይህ ልጅ በአባት ቤት እያለ በምን አይነት መንገድ ጠፍቶ እንደነበረ አስረዳ? ይህ ምሳሌ ለፈሪሳዊያን ምን መልዕክት ነበረው? አባትየው ለታላቁ ልጅ ያለው ትምህርት ምን ነበር? ከዚህ ስለ እግዚአብሔር ባህሪ ምን ትረዳለህ?

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

8. የጠፋነውን እኛን ለመፈለግ ከሰማያት የወረደውን ጌታ ባገኘንም ጊዜ በሰማይ ታላቅ ደስታ ያደረገውን ጌታ ፍቅርን፣ የምህረቱን ስፋትና ጥልቀት ስታይ ለእርሱ ያለህን መስጠትና አምልኮ እንዴት ልትገልፀው ወሰንክ?
9. ጌታ ለጠፋው ያለውን ፍቅር፣ ትዕግስትና ምህረት ስትመለከት አንተስ አሁን ለጠፉት ልዩ ፍቅር፣ ትዕግስትና ምህረት ልትሞላና ዘወትር ልትፀልይ እንደሚገባህ ተረዳህ?
10. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

በመመለስና በማረፍ የሚያድነው ጌታ ዛሬም ለጠፉት እጅግ ግድ ይለዋል። ይህንን ታላቅ ፍቅርና ምህረት ግን በእኛ ውስጥ የማስታረቅ ቃልንና መንፈስን በማኖር ለፈፅመው እኛን ወደ ቤቱ ጠርቶናል። እንግዲህ እኛም የጠፉት ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲመለሱና በእግዚአብሔር አባትነት እንዲጠለሉ ዘወትር ልንተጋ ይገባል።

### የቃል ጥናት

"እላችኋለሁ እንዲሁ ንስሃ ከሚያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ፃድቃን ይልቅ ንስሃ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ታላቅ ደስታ ይሆናል።" ሉቃ 15:7

## ጥናት 42

## የብልጉ መጋቢ ምሳሌነት

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 16:1-19

### መግቢያ

በባለፈው ጥናት የእግዚአብሔርን አባትነት በምሳሌ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ስለ አንድ አባካኝና መጋቢ ልባምነት በምሳሌ ያስተማረውን እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ. 1-2 ላይ የኃላፊነት አደራ የተሰጠው ይህ መጋቢ (ሥራ አስኪያጅ) ሥራውን እንዴት እየተወጣ እንደሆነ ግለጽ። ባለጠጋው ለዚህ ሰው ምን አለው? የመጋቢውስ ምላሽ ምን ነበር? ከዚያስ ምን ለማድረግ በልቡ ወሰነ?

2. ከቁ 5-7 ባለው ክፍል ውስጥ ይህ መጋቢ ምን አደረገ? ያደረገው ትክክል ነበርን? የጌታው ምላሽ ምን ነበር? ለምን?

3. በዚህ ምሳሌ ውስጥ የጌታ ዋና ሀሳብ (ሊያስተምራቸው የፈለገው) ምንድን ነበር ትላለህ? ቁ 5-11

4. በቁ.11 ላይ ኢየሱስ “. . . እውነተኛውን ገንዘብ” ሲል ምን ማለቱ ነው? ከምሳሌው ጋር በማነፃፀር ተወያዩበት። የአመፃውስ ገንዘብ?

5. ይህንን ምሳሌ የሰሙት ፈሪሳዊያን ምላሻቸው ምን ነበር? ለምን? ቁ.14-15 ምናልባት እነርሱም ገንዘብ ወዳጆች ስለነበሩ የአራጣ ብድር ሥራ ላይ ተሠማርተው ይሆንን?
6. በክፍሉ ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ሲያስተምር “ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ባሪያ ማንም የለም” (ቁ.13) ካለ በኋላ “ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።” (ቁ. 13) ብሎ በአፅኖት ሲናገራቸው እንመለከታለን። ገንዘብ የሰው ጌታ መሆን የሚጀምረው መቼ ነው?

### የማዛመድ ጥያቄዎች

7. በተሰጠህ ትንሽ አደራ (ኃላፊነት) ላይ ምን ያህል ታማኝ ነህ?
8. አላፊ በሆነው ምድራዊ ገንዘብና ሀብት ለችግረኞችና ለሚያስፈልጋቸው መስጠትና ማካፈል የዘላለም ትርፍ እንደሚያስገኝ ተረዳህ?
9. በጥቂቱ የሚታመን በብዙ እንደሚሾም እንዲሁም በተሰጠህ አደራ በታማኝነት በትጋት መፈፀም በሌላ በትልቅ ኃላፊነት ላይ መሾምን እንደሚያመጣልህ ተረዳህን?
10. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### ማጠቃለያ

ጌታ ኢየሱስ በዚህ ምሳሌ በተሰጠው አደራ ላይ በማመፅ ያልተፈቀደልትን ነገር ግን በልባምነት ያደረገውን ሥራ አስኪያጅ ጌታው እንዳመሰገነው አይተናል። በተጨማሪም በጥቂቱ የሚታመን በብዙ ደግሞ እንደሚታመን እንማራለን። እኛም በተሰጠን ማንኛውም አደራ ላይ ኃላፊነታችንን ለመፈፀም በታማኝነት እንትጋ። እውነተኛና የዘላለምን ሽልማትን ያስገኝልናልና።

### የቃል ጥናት

“ከሁሉ በሚያንስ የታመነ በብዙ ደግሞ የታመነ ነው።” ሉቃ 16:10

# ጥናት 43

## የባለጠጋውና የአልዐዛር ምሳሌ

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 16:20-31

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት አባካኝ መጋቢ (ሥራ አስኪያጅ) መልባምነት ስላደረገው ሥራ ተመልክተን ነበር። በዛሬው ጥናት ደግሞ የአንድ በጌታ ያይደለ ምድራዊ ባለጠጋ ጅማሬና ፍፃሜ እንዲሁም በጌታ ሆኖ በድህነት፣ በብዙ ችግርና ስቃይ ምድራዊውና ጊዜያዊ ሕይወቱን ስላሳለፈው በመጨረሻ ግን የዘላለምን ሕይወት ወራሽ ስለሆነው አልዐዛር ምሳሌ እናያለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ባለጠጋው በቁ. 19 በምን ዓይነት ኑሮ ላይ ነበር? ልብሱ ምን ይገልፃል? አልዐዛርስ? (20-21) ውሾች ምን ያደርጉለት ነበር? ሰውስ?
2. አልዓዛር ከሞተ በኋላ መጨረሻው ምን ነበር? የባለጠጋውስ?
3. በቁ. 23-24 ባለጠጋው አብረሃምን ምን ብሎ ጠየቀው? የአብረሃምስ ምላሽ ምን ነበር? ከዚህስ ምን እንማራለን? ተወያዩበት።
4. በቁ. 27-28 ላይ ባለጠጋው በሕይወት ሳለ ያላሰበላቸውን ወንድሞች ከሞተ በኋላ ሲጨነቅላቸው እናያለን። ከዚህ የተነሳ አብረሃምን ምን ጠየቀው? የአብረሃምስ ምላሽ?
5. “ሙሴና ነብያትን ካልሰሙ ከሙታን አንዱ ቢነሳም አያምንም” ያለው ለምን ይመስልሃል? ኢየሱስ በዚህ ሊያሳያቸው የፈለገው ምንድን ነው? ተወያዩበት። የአሁኑ ዘመን ሙሴና ነብያት እነማን ናቸው?

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

6. በመንፈስ ድሆች ለሆኑ በክርስቶስ ላመኑ ፃድቃን እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ብድራት አስተዋልክን?
7. ባላቸው ጊዜያዊ ሀብት፣ ብልጥግናና ምቾት ተታልለው ዘላለማዊውን ለዘነጉ ምን ያህል ትፀልያለህ? ለእነሱ ሙሴና ነብይ እንደሆንክ ታስተውላለህን? ሊመጣ ያለውን ዘላለማዊ ፍርድና ጥፋት በፍቅርና በድፍረት ትመሰክራለህን?
8. በአጠቃላይ ከዛሬው ምሳሌ ምን ተማርክ? ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ያስተማረበት ዋና ሀሳብ ምን ነበር? የተማርከውን ለቡድኑ አካፈል።

### *ማጠቃለያ*

መጽሐፍ ቅዱሳችን በክርስቶስ በማመናችን ምክንያት የተዘጋጀልንን የዘላለም ህይወት ዋስትና እንጂ በምድር ላይ ሊደርስብን ወይንም ልናልፍበት ስለምንችለው ጊዜያዊ ችግርና በሽታ መከላከያ (ዋስትና) አልሰጠንም። ስለዚህ ከሁሉ አስቀድመን ከምናልፍበት ምድራዊ (ጊዘያዊ) የኑሮ ከፍታና ዝቅታ ባሻገር በሰማይ ሊኖረን ስላለው ሀብትና የዘላለም ሕይወት ልንሰራና ልንተጋ ይገባናል። ድሆችን መርዳትና በበሽታቸው መራራት የአማኞች ሁሉ የሥራ ድርሻ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም። እምነታችን በሥራ መገለጥ አለበትና። ያዕ 2:26 ፤ ያዕ 1፡27

### የቃል ጥናት

“ሙሴና ነብያትን ካልሰሙ ከሙታን አንድ ቢነሳም አያምኑም።” ሉቃ 16:31

# ጥናት 44

## ይቅርታ፣ እምነትና ምስጋና

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 17፡1-19

### መግቢያ

በባለፈው ጥናት ስለባለጠጋውና ስለአልዐዛር ምሳሌ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ተበድለን ይቅር ስለማለት እና እምነት ስላለው ሀይል እንዲሁም ስለተደረገልን ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባን እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በቁ. 2 ላይ ኢየሱስ ለሰዎች ማሰናከያ እንዳይሆኑ ለሐዋሪያት በንፅፅር ያስተማራቸው ምን ነበር? ማቴ፡-5:29-30 ፤ ማቴ፡-18:6

2. ቁጥር 3 እና 4ን ኢየሱስ ሲያስተምር ከወንድሞች ጋር በሚኖረን ህብረት ማድረግ ስለሚገባን ነገሮች የተናገረውን በዝርዝር ተወያዩበት። ማቴ፡-18:15-17 ፤ ኤፌ፡-4:32 ፤ ቆላ፡-3:13

3. ከቁ. 5-6 ላይ ሐዋሪያት "እምነትን ጨምርልን" ብለው ሲጠይቁት ኢየሱስ ምን መልስ ሰጣቸው? "የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል" ሲል ምን ማለቱ ነው? ማቴ 13:31 ፤ ማቴ 21:12

4. ኢየሱስ እስከመጨረሻው ድረስ የቤቱን ባለቤት ሊያገለግል ስለሚገባው አገልጋይ የተናገረው ምሳሌ ምን መልዕክት ለማስተላለፍ ነው? ሉቃ 12:37 ፤ 1ቆሮ 9:18 ፤ ማቴ 6:5
5. በቁ. 11-17 ኢየሱስ በሰማሪያና በገሊላ መሀከል ሲያልፍ የስጋ ደዌ ህሙማን እንደፈወሰ ይናገራል።
   - ሀ. የተፈወሱት መቼ ነው?
   - ለ. ስለምን ራሳችሁን ለካህን አሳዩ አለ? ዘሌ 13:1-8
   - ሐ. እግዚአብሔርን እያከበረ የተመለሰውን ሳምራዊ ኢየሱስ ምን ሲል ጠየቀው?
   - መ. ለምስጋና ያልተመለሱትን ተመልሶ መጥቶ ካመሰገነው ጋር ያላቸውን የህይወት ልዩነት ተወያዩበት።

### የማዛመድ ጥያቄዎች

6. በቃልና በተግባር የምናደርጋቸው ነገሮች የሰዎችን ህይውት እንዳያሰናክሉና የእግዚአብሔርን ማንነት የሚሸፍኑ እንዳይሆኑ በጥንቃቄ መመላለስ እንድንችል ምን ማድረግ ይኖርብናል?
7. ሰዎች በፀፀት ይቅርታን ሲጠይቁን እኛም በተመሳሳዩ ከእግዚአብሔር ብዙ ምህረትና ይቅርታን እንዳገኘን አስበን ምን ያህል ይቅርታን ለማድረግ የተፈታና የተዘጋጅ ልብ አለን?
8. በከበረ ዋጋ የተገዛንና የኃጢአታችን ዋጋ የተከፈለልን መሆኑን አውቀን የምስራቹን ወንጌል በመስበክና በማገልገል ትጋታችን ምን ያህል አጥጋቢ ነው ትላለህ?
9. በነገር ሁሉ እግዚአብሔር አባታችንን በልጁ በኢየሱስ በኩል ማመስገን እንዳለብን ተገንዝበሃልን? ኤፌ 5:20
10. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### ማጠቃለያ

በተግባርና በቃል በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት ካለነቀፋ በእምነት እንመላለስ። በምህረቱና ቸርነቱ ተጎብኝተን የተቀበልነውን ሕይወት እኛም የይቅርታ ልብ ይዘን በስራ (በምግባር) እንግለፀው። ከእኛ የሆነ ወይንም ከጌታ ያልተቀበልነው የለምና በምስጋና የተሞላ የአምልኮ ህይወት ሊኖረን ይገባል።

### የቃል ጥናት

"ወንድምህ ቢበድልህ ገስፀው ቢፀፀትም ይቅር በለው" ሉቃ 17:3

# ጥናት 45

## የእግዚአብሔር መንግስት መምጣት

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 17:20-37

### መግቢያ

ባለፈው ጥናት ተበድለን ይቅር ስለማለት እና እምነት ስላለው ሐይልና ጉልበት እንዲሁም ስላደረገልን ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባን ተምረናል። በዛሬው ጥናት ስለ እግዚአብሔር መንግስት መምጣትና ስለመነጠቅ እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ጌታ ኢየሱስ በቁ. 17 ላይ "የእግዚአብሔር መንግስት በመጠባባቅ አትመጣም . . . እነሆ የእግዚአብሔር መንግስት በመካከላችሁ ናትና" ሲል ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?
2. ከቁ. 20-24 ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር መንግስት ተጠይቆ የሰጠውን መልስ አብራራ።
3. ከቁ. 26-27 ኢየሱስ "በኖህ ዘመን እንደሆነ ሁሉ በሰው ልጅ ዘመንም እንዲሁ ይሆናል" ብሎ ሲናገር ምን ማለቱ ነው? ዘፍ 6:5-6፤ ዘፍ 7:1-5
4. በቁ. 28-29 "በሎጥ ዘመን እንዲሁ ነበር" ሲል በሎጥ ዘመን የነበረው ህዝብ ምን ይመስል እንደ ነበር ግለፅ። ዘፍ 18:20-21
5. ቁ.30-37 ክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም በሚገለጥበት ቀን ስለሚሆነው መነጠቅ አስረዳ። ራዕ 1:7 ፤ 2ተሰ 1:7

### የማዘመድ ጥያቄዎች

6. የእግዚአብሔርን መንግስት ዓላማ በህይወታችን በተግባር እንዲታይ ምን ያህል እንጥራለን?
7. የኖህና የሎጥ ዘመን ሰዎች ከኃጢአት የተነሳ እንደጠፉ ዛሬም በዚህ ዘመን ካለማመን የተነሳ ወደ ጥፋት ስለሚነዱ ወገኖቻችን ምን ያህል ግድ ይልሃል?
8. የክርስቶስ ኢየሱስ መምጫው ከመቼውም ጊዜ ይልቅ እንደቀረበ አውቀን ኑሮአችን ተግባራችንና ዕቅዳችን በዚህ ሀሳብ የተቃኘ ነውን?

### ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር መንግስት ዓላማ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሥራ ከኖህና ከሎጥ ዘመን ይልቅ እጅግ የከፋውን ቅጣት ሊያስመልጥ ስለሆነ እኛም ሌሎች ሰዎች እንዲያመልጡ የመንግስቱን የምስራች እንደ አንድ አዋጅ ነጋሪ ሆነን ልንናገር ሙሉ ሀላፊነት እንዳለብን ልንገነዘብ ይገባናል።

### የቃል ጥናት

"ነፍሱን ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፤ ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ በህይወት ይጠብቃታል" ሉቃ 17:32

# ጥናት 46

## ሕፃናትና ባለ ጠጎች በእግዚአብሔር መንግስት

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 18:15-30

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት የእግዚአብሔር መንግስት መምጣትና ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ ስለሚሆነው የቅዱሳን መነጠቅ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ኢየሱስ ሕፃናትን አስመልክቶ ስላስተማረው እንዲሁም ባለፀጋ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ጭንቅ እንደሚሆንበት ያስተማረውን እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ቁ.17 "የእግዚአብሔር መንግስት እንደ ህፃናት የማይቀበል ሁሉ ከቶ አይገባባትም" ሲል ምን ማለቱ ነው? ማቴ 11:25-26፤ ማቴ 18:1-4
2. ቁ. 18 ኢየሱስ "የዘላለምን ህይወት እንዳገኝ ምን ላድርግ?" ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠውን መልስ አብራራ።
3. የኢየሱስ ምላሽ በአለቃው ዘንድ ምን ስሜት ፈጠረ? የጠየቀው የዘላለም ሕይወት ሆኖ ሳለ የምድራዊውን ነገር ለመልቀቅ አለመፈለጉ ምን ያሳያል?
4. ቁ. 23-25 ስለምን ብዙ ሀብት ያለው ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት ጭንቅ ይሆንበታል? 1ጢሞ 6:10 ፤ ዕብ 13:5 ፤ ምሳ 11:28
5. ቁ. 29-30 ስለ እግዚአብሔር መንግስት ብሎ ዋጋን መክፈል ብድራቱስ ምን ይሆን? ዕብ 11:24-27

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

6. ሰዎች የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኙና የእግዚአብሔር መንግስት እንዲስፋፋ ምን እያደረግህ ነው?
7. አንድ ሰው የዘላለም ሕይወት አገኝ ዘንድ ምን ላድርግ ቢልህ ከእግዚአብሔር ቃል ምን መልስ ትሰጠዋለህ?
8. በድካሜ ዋጋ አገኘሁኝ በምትለው ገንዘብና ሀብት ላይ ምን ያህል የእግዚአብሔር ቃል ባለስልጣን እንዲሆን ሾመህበታል?
9. በክርስትና ሕይወታቸው እንደ ኢየሱስ ደቀመዛሙርት ሁሉን ትተው መከተል አቅቶአቸው የሚንገዳገዱ ወገኖች ቢያጋጥሙህ በቃሉ የተደገፈ ምን ምክር ይኖርሃል?
10. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

በዚህ ዓለም ሀሳብ ያልተበረዘ ልክ እንደ ሕፃናት ንፅሁ የሆነ ልብን ይዘን የእግዚአብሔርን መንግስት ለማስፋፋት ጌታ በሰጠን ሀብትና ንብረት እንዲሁም ማንኛውም ነገር ሁሉ እንደታማኝ አገልጋይ በኑሮአችን እግዚአብሔርን እያከበርን ልንኖር ይገባናል።

### *የቃል ጥናት*

"በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል" ሉቃ 18:27

## ጥናት 47

## በርጠሜዎስና ዘኪዎስ

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 18:31-43፤ 19:1-10

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ኢየሱስ ሕፃናትን አስመልክቶ ስላስተማረው እንዲሁም ባላፀጋ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ጭንቅ እንደሚሆንበት ያስተማረውን ተመልከተናል። በዛሬው ጥናት ኢየሱስ ስለሞቱ ዳግመኛ ስለመናገሩና በኢያሪኮ አቅራቢያ ዐይነ ስውሩ በርጠሜዎስን እንዴት እንደፈወሰው እንዲሁም ስለ ዘኪዎስ ታሪክ እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ቁ. 31-34 ኢየሱስ በነብያት ስለእርሱ የተፃፈው ሁሉ እንደሚፈፀም ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸው ምንድን ነው? ኢሳ 53 ተመልከት።

2. ቀ. 34 ለደቀ መዛሙርቱ ስለእርሱ በነብያት የተፃፈውን ትንቢት ቢነግራቸውም አላስተዋሉም፣ የተናገረውም አልገባቸውም ነበር። ይህ ከምን የተነሳ ነው ትላለህ? ኤፌ 5:15-17፤ 2ጢሞ 2:7 ፤ 1ዮሐ 5:20

3. ቁ.37-39 ኢየሱስ በዚህ ክፍል "የናዝሬት" እና "የዳዊት ልጅ" ተብሎ ሲጠራ እናያለን። ይህ ከምን የተነሳ ነው? ሉቃ 1:26-27፤ ሉቃ 2፡ 4-7

4. በቁ. 35-43 ላይ ባለው ታሪክ መሠረት የበርጠሜዎስን (ማር 10:46) እምነት የሚያሳዩ ምን ተግባራት አስተዋልክ?

5. በም. 19:1-10 ባለው ታሪክ መሠረት ጌታ ኢየሱስ በዘኪዎስ ቤት ተገኝቶ "ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታልና" እንዲል ያሰኘው የዘኪዎስ ድርጊት ምንድን ነው?

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

6. በእግዚአብሔር ቃል የምናያቸው ትንቢቶች ሊፈፀሙ ግድ ነው። ምን ያህል ካለቸልተኝነት በትጋት እንጠብቃቸዋለን?
7. በርጠሜዎስ ስለ ጌታ መረዳት ያለው ሰው ከመሆኑ የተነሳ እንደሚፈወስ አምኖ ሰዎች ቢከለክሉትም በብዙ ጩኸት ከጌታ ፈውስን ለመቀበል ችሎአል። እኛስ ዛሬ በፀሎት ህይወት ወደጌታ አጥበቀን በመጮህ እንፀልያለን? ከጌታስ አዘውትረን በመፀለይ የተቀበልነው አለን?
8. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

ትንቢት የፀና የእግዚአብሔር ቃል ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ዘመኑን ሁሉ የሚዋጁ ትንቢቶች ለየጊዜው አሉ። እነዚህን ትንቢቶች እየመረመርን ከግል ህይወታችን ጀምሮ ላሉ ማንኛውም ጉዳዮች በእምነት ልንጠብቃቸው ይገባናል። እምነታችን በምልክቶች በታአምራትና በድንቃ ድንቆች ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን ምድርና ሰማይን ባፀናው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሊሆን ይገባዋል።

### የቃል ጥናት

"እይ፤ እምነትህ አድኖሃል" ሉቃ 18:42

# ጥናት 48

## የአስሩ ምናን ምሳሌ

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 19፡11-27

### መግቢያ

ባለፈው ጥናት ስለ ዕውሩ ስለነበረው በርጠሜዎስና ስለ ዘኪዎስ ታሪክ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በሚያደርገው ጉዞ ላይ አብረውት ለሚጓዙት ተከታዮች የእግዚአብሔር መንግስት ባለአደራዎች እንደሆኑና አደራውንም ተቀብለው ለሚያመጡት ውጤት ያለውን ምላሽ ሲያስረዳቸው እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቁ.11 - ኢየሱስን የሚከተለው ሕዝብ ስለ እግዚአብሔር መንግስት ምን ዓይነት መረዳት ነበራቸው?

2. ንጉሳዊ ስልጣን ተረክሞ ለመመለስ ወደሩቅ ሀገር የሚሄደው መስፍን የሀገሩ ሕዝብ ለምን ጠሉት? በቁ 14 የሀገሩ ሕዝብ ንጉስ ሆኖ የመጣውን መኮንን ለምን ጠሉት?

3. አንድ ምናን የተቀበለው ሰው ለምን ቀበረው? ከዚህ ሁኔታ የወንጌልን አደራ እንደሚገባ ለመወጣት በመጀመሪያ ምን መረዳት ያስፈልጋል ትላለህ?

4. የተሰጠውን አንድ ምናን (ገንዘብ) ቀብሮ ካስቀመጠው አገልጋይ ያው ያለው ተነጥቆ ለሌላ ብዙ ላተረፈው መሰጠቱ ምን የሚያስተምረን ነገር አለ?

5. በላያቸው እንዲነግስ እንቢ ያሉትስ ፍፃሜ ምን ሆነ? ኢየሱስን የማይቀበሉና የሚንቁ ፍፃሜያቸው ምን ይሆናል?

### የማዛመድ ጥያቄዎች

6. እስኪመጣ ድረስ ጌታ ኢየሱስ የሰጠን አደራ ምንድን ነው? እንዴትስ እየተወጣነው ነው? የተሰጠንን አደራ ሳንወጣ መቅረት የሚያስከትለውን ውጤት ስታይ ምን እንድታደርግ ይገፋፋሃል?
7. በተሰጠን ሥጦታ ነግደን ለማትረፍ የምንችለው እንዴት ነው?
8. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### ማጠቃለያ

ወደ እግዚአብሔር መንግስት የተጠራነው ዘላለማዊ ሕይውትና መንፈሳዊ በረከትን እንድንቀበል ብቻ ሳይሆን በሕይወታችን ያየነውንና የተለማመድነውን ሁሉ እንደ ሕያዋን ምስክሮች ሆነን ለዓለም እንድናበስር ነው። "አንተ ክፉ አገልጋይ" እንደተባለው አደራችንን ቀብረን ልናስቀምጠው ሳይሆን ይልቁንም አብልጠን ጌታን በማገልገል የተሰጠንን መክሊት እንድናተርፍበት ይገባል። ዛሬ ብዙዎቻችን ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን አደራ ይዘን ተኝተናል። ከእንቅልፍ የምንነቃበት ዘመኑ እንደደረሰ አሁን አውቅን የተሰጠንን አደራ ልንፈፅ ልንተጋ ይገባል። (ሮሜ 13፡11)

### የቃል ጥናት

"ላለው ሁሉ ይሰጠዋል፤ ለሌለው ግን ያው ያለው እንኳን ይውሰድበታል" ሉቃ 19፡26

# ጥናት 49

## ሆሳህና

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 19:28-44፤ 13:31-35

### መግቢያ

ባለፈው ጥናታት ስለእግዚአሔር መንግስት ለሌሎች የማስተላለፍ አደራ ለሁላችንም እንደተሰጠን ዳግመኛም እስኪመጣም ድረስ መነገድና ማትረፍ እንዳለብን ተመልከተናል። በዛሬው ጥናት ደግሞ ጌታችን በምን ዓይነት ሁኔታ ወደ ኢየሩሳሌም ለመጨረሻ ጊዜ እንደገባ እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቁ.28-31 ኢየሱስ ወደ ቤተፋጌና ቢታንያ ከተሞች በቀረበ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱስ ምን ትዕዛዝ ሰጣቸው? ከትዕዛዙ ምን ተማርክ?

2. ከ32-34 እግዚአብሔር በሚሰራበት ቀን እንዲጠቀምበት ንብረታቸውን "ጌታ ይፈልገዋል" ስለተባሉ አለመከልከላቸውን ስታይ ስለባለቤቶቹ ምን ግንዛቤ ወሰድክ?

3. ቁ.30 - ጌታ ኢየሱስ ስለምን ማንም ያልተቀመጠባትን ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ለመግባት መረጠ? ዘካ 9:9ን በማንበብ ተወያዩበት።

4. ቁ. 37-39 - ደቀ መዛሙርት በደስታ እየጮሁ ሲያመሰግኑት በሌላው ወገን ምን ዓይነት ሰዎች ተነሱ? ይህስ በምስጋናቸው ላይ ያመጣው ተፅኖ ነበር?

5. ቁ. 40 - "እነርሱ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮሃሉ" ሲል የእግዚአብሔር ሃሳብ ሊፈፀም ግድ እንደሆነ ሀሳቡም እንደማይከለከል ከዚህ አልተረዳህምን?
6. ቁ.41-44 ተከታዮቹ ስለእርሱ በደስታ እየዘመሩ ጌታ ኢየሱስ ግን ስለ ኢየሩሳሌም ያለቅስ የነበረው ለምንድ ነው?

7. ቁ.44 - ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ከተማ ወደ ፊት ሊደርስ ያለውን ሲናገር "የመጎብኘትሽን ጊዜ አላወቅሽም" ሲል ምን ለማለት ፈልጎ እንደሆነ አስረዳ።

### የማዛመድ ጥያቄዎች

8. እንደውርንጫው ባለቤቶች ለጌታ ስራ የሚያስፈልገውን ለመስጠት ምን ያህል ዝግጁዎች ነን።
9. በተቃሚዎች ፊት ምን ያህል ጌታን እናከብረዋለን።
10. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል ኢየሱስ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ለንጉስ በሚደረግ አቀባበል እንደገባ አይተናል። 2ነገ 9:13 ይህም በዳዊት ዙፋን ላይ እንደሚቀመጥ በነብያት የተነገረውን በይፋ የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር የተናገረውን የሚፈፅም፣ በቃሉ ታማኝ አምላክ መሆኑን በአጽኖት አይተናል። ለጌታ የሚያስፈልገው ውርንጫም እንደሚዘጋጅ፤ ለክብሩ የሚዘምር ባይኖር ድንጋዮች ተነስተው እንደሚዘምሩ በማወቅ እኛም እግዚአብሔር በሚሰራበት ቀን ገንዘቡ ሆነን እንድንገኝ ዝግጁ ልንሆን ያሻል።

### የቃል ጥናት

"ማንም ፦ ስለምን ትፈቱታላችሁ? ብሎ ቢጠይቃችሁ፤ እንዲሁ፦ ለጌታ ያስፈልገዋል በሉ አላቸው።" ሉቃ 19:31

# ጥናት 50

## ግንበኞች የናቁት ድንጋይ የማዕዘን ራስ ሆነ

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 19:45-48፤ 20:1-47

### መግቢያ

ባለፈው ጥናት ኢየሱስ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ለመጨረሻ እንደገባ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ቤተመቅደሱ የፀሎት ቤት እንጂ የወንበዴዎች ዋሻ አለመሆኑን በስልጣን ካረጋገጠላቸው በኋላ የሐይማኖት አለቆች ሊገድሉት እንደፈለጉ አለቆችና ጽሐፍት እንዴት በጥያቄዎች ሊያጠምዱት እንደሞከሩ እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ም. 19:45-46 ጌታ ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚሸቅጡትና የሚገዙትን ለምን አስወጣ? ተወያዩበት።
2. ቁ.2 በመመልከት የካህናት አለቆችና ፃፎች ከሽማግሌዎች ጋር ወደ እርሱ ቀርበው የጠየቁት ጥያቄ ምንድን ነበር? ጌታ ኢየሱስ እንዴት መለሰላቸው?
3. ከቁ. 9-18 ኢየሱስ አንድ የወይን እርሻ ባለቤትና ገበሬዎችን በመጥቀስ ለሕዝብ በምሳሌ ሲያስተምር እንመለከታለን።
   - ሀ. በምሳሌው ውስጥ እነማን ተጠቅሰዋል? የእያንዳንዱ ምሳሌነት ምንድን ነው?
   - ለ. የወይኑ እርሻ ባለቤት የላካቸውን አገልጋዮች ያልተቀበሉበት ምክንያት ምን ይመስልሃል? ይህ ስለ ገበሬዎቹ ልበ ደንዳናነት ምን ይነግረሃል?
   - ለ. ገበሬዎቹ ልጁን ምን አደረጉት?
   - ሐ. የወይኑ እርሻ ባለቤት ከዚህ ሁሉ በኋላ ምን እርምጃ ወሰደ?
   - መ. ኢየሱስ በዚህ ምሳሌ ሊያስተላልፍ የፈለገው አብይ መልዕክት ምንድን ነው?

4. ከአፉ በሚወጣው ቃል ሊያጠምዱት የተላኩ ሸማቂዎች "ለቄሳር ግብር መክፈል ተፈቅዷልን ወይስ አልተፈቀደም?" ብለው ሲጠይቁት ምን መልስ ሰጣቸው? አንተስ ከዚህ ምን ትማራለህ?
5. ሰዱቃዊያን እነማን ናቸው? ኢየሱስ ለሰዱቃዊያን የመለሰው መልስ ምንድን ነው? ስለ ሙታን ትንሳኤ የሰጠውን ሀሳብ አብራራ።
6. ኢየሱስ በመዝ 118:32 ላይ ያለውን ቃል በመጥቀስ የዳዊት ልጅ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ ጌታ መሆኑን የገለፀበትን ሀሳብ በዝርዝር ተወያዩበት።
7. በቁ. 45-47 ኢየሱስ ስለፃፎች ማንነት ለህዝቡ ምን አስረዳ?

### የማዛመድ ጥያቄዎች

8. ኢየሱስ በቤተመቅደስ የነበሩትን የሸቃጮችን መደብ እንግለበጠና የሚሸጡና የሚገዙትን እንዳስወጣ እኛም ለእግዚአብሔር ቤት በመቅናት ምን ያህል እንተጋለን?
9. ሰዎች ጻድቃን መስለው በክፉ ጥያቄዎች ሊያጠምዱህ ሲሹ አንተ በእግዚአብሔር ቃል ለመመለስ ምን ያህል ዝግጁ ነህ?
10. ለታይታ ከሚደረጉ የግብዝነት ተግባሮች ምን ያህል ራሳችንን እንጥብቃለን?

### ማጠቃለያ

ኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር ሳይቆጥር የባሪያን መልክ ይዞ በሰዎች መካከል ተመላለሰ። ወደ ገዛ ወገኖቹ አስቀድሞ ቢሄድም ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም። እርሱ ግን የማዕዘን ራስ ሆኖ በሞቱ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አስታረቀን። ዛሬም ለእኛ ለምናምን የዘላለም ሕይወት፣ ለማይቀበሉት ግን የዘላለም ጥፋት ነው።

### የቃል ጥናት

"ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ።" ሉቃ 20:17

# ጥናት 51

## የዘመኑ መጨረሻ ምልክቶች

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 21፡1-38

### መግቢያ

ባለፈው ጥናት ጌታ ኢየሱስ በቤተመቅደስ ውስጥ የነበሩትን ሸቃጮች እንዳስወጣና እርሱ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ የማዕዘን እራስ እንደሆነ ተመልክተናል። ጌታ ኢየሱስ በመጨረሻ የምድር ላይ አገልግሎቱ ከተናገራቸው አንዱ ስለ መጨረሻው ዘመንና ምልክቶች ነበር። ዛሬም ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ምን ያህል ቀኑ እንደቀረበ በመረዳት ይህንን ጥናት እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቁ. 1-4 ኢየሱስ ሁለት ሳንቲም የሰጠችውን መበለት ከሁሉ በላይ አብልጣ መስጠቷን መስከሯል። ይህን ያለበት ምክንያት ምንድን ነው?

2. ከቁ. 10-28 ኢየሱስ የመጨረሻ ዘመን ምልክቶች ምን እንደሆኑ በዝርዝር ተናግሯል።

    ሀ. ከቁ. 5-9 ባለው ክፍል የተገለፁትን ምልክቶችን ዘርዝር። እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ የሚመጡትን ሀሰተኞች በተመለከት የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው? ተወያዩበት።
    ለ. ከቁ. 10-19 ባለው ክፍል የተገለፁትን ምልክቶች በተለይም ስለ ስሙ በወኅኒ ስለ መጣልና በገዢዎች ፊት ስለመቆም የሰጠውን ሀሳብ በመግለጽ ተወያዩበት።
    ሐ. ከቁ. 20-24 በኢየሩሳሌም ላይ ስለሚደርስ መከራ ኢየሱስ የተናገረውን ተወያዩበት።
    መ. ከ25-28 በምድርና በሰማይ ላይ የሚታዩን ምልክቶች ግለጽ።

3. በቁ. 32 ላይ "ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም" ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. በዘመን መጨረሻ ከሚመጡ የጥፋት ምልክቶች ተጠብቀን በሰው ልጅ ፊት በጽድቅ እንድንቆም ምን ማድረግ ይኖርብናል?

### የማዛመድ ጥያቄዎች

5. ጌታ የሚያየው የልብን ሲሆን ሰው ግን የሚያየው የውጭውን ነው። ስጦታችን ከምን ዓይነት ልብ የሚወጣ ሊሆን ይገባዋል?
6. የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች ምን ያህል እየተፈፀሙ እንዳለ ስታይ ምን ያህል ጌታን በመጠባበቅ ሕይወት ውስጥ ትገኛለህ?
7. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### ማጠቃለያ

ይህን ክፍል ስናይ ያለንበት ዘመን የመጨረሻ ዘመን ብቻ ሳይሆን ለመጨረሻው የመጨረሻ እንደሆነ እናስተውላለን። በዚህ ዘመን ከምንም ጊዜ በላይ የጌታ መምጫ ምልክቶች እየታዩ ነው። ዘመኑ ምንም እንኳን እየከፋ ቢሄድም መሸሸጊያችን ሐያሉ እግዚአብሔር ነው። እኛም ሸክምን ሁሉ፣ የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን የእምነታችን ራስና ፈፃሚውን ኢየሱስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግስት እንሩጥ።

### የቃል ጥናት

"እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ፤ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትፀልዩ ትጉ" ሉቃ 21፡36

# ጥናት 52

## የመጨረሻው እራት

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 22:1-38

***መግቢያ***

ባለፈው ጥናት በዘመነ ፍፃሜ በምድርና በሰማይ ስለሚታዩ ምልክቶች ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን አልፎ በሚሰጥባት ፈታኝ በሆነ ሌሊት ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የመጨረሻውን እራት አብሮ ሲበላና በእራቱ ወቅት በማዕድ ከርሱ ጋር ለነበሩት ደቀመዛሙርት የሚሰጣቸውን ምክሮች እናያለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በዘፀ 12፡5-11 ላይ ከተፃፈው በመነሳት እስራኤላዊያን የቂጣን በዓል (ፋሲካን) ማክበር የጀመሩበትን ጊዜና ሁኔታ አስረዳ? ፋሲካ በእስራኤላዊያን ዘንድ የሚከበረው እንዴት ነው? ፋሲካ ማለት ምን ማለት ነው?

2. በጊዜው የነበሩት የሃይማኖት መሪዎች ጌታን ሊገድሉ በየጊዜው ቢፈልጉም ይፈሩ የነበረው ማንን ነበር? ኢየሱስ ሲፈልጉት ለነበሩት የሃይማኖት መሪዎች እንዴት አሳልፎ ተሰጠ? ይህንን ያነሳሳው ምንድን ነበር?

3. ኢየሱስ በቁ. 15 "ከመከራዬ በፊት ከእናንተ ጋር ይህን ፋሲካ ልበላ እጅግ እመኝ ነበር" በማለት በዚህ ማዕድ ላይ ፍቅሩን ለደቀመዛሙርቱ ያሳየባቸውን መንገዶች ዮሐ 13፡1-10 በመልከት ተወያዩበት።

4. ኢየሱስ በቁ. 16 "የእግዚአብሔር መንግስት እስኪፈፀም ድረስ ወደ ፊት ከዚህ አልበላም" ሲል ምን ማለቱ ነው?

5. ከቁ 24 -27 በደቀመዛሙርት መካከል የነበረው ክርክር ምን ነበር? ኢየሱስ ምን ብሎ አስተማራቸው? ተወያዩበት።

6. በክፍሉ ውስጥ ለጴጥሮስ እምነቱ እንዳይጠፋ "ማለድኩልህ" ሲለው ይሁዳን ደግሞ "ለዚያ ሰው ወዮለት" ይላል። ይህንን ልዩነት የፈጠረው ምን ይመስልሃል።

***የማዛመድ ጥያቄዎች***

7. ኢየሱስ እንጀራውን አንስቶ "ስለ እናንተ የሚሰጠው ስጋዬ ነው" ጽዋውንም አንስቶ "በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው" ብሎ ለመታሰቢያዬ አድርጉት አላቸው። የኢየሱስ መስዋዕትነት ላአንተ (ላንቺ) መሆኑን ተረድተህ ዘወትር ታስበዋለህ?
8. በእግዚአብሔር ፊት ትልቅ የሚያደርገን እርስ በእርስ መዋደድና ሌሎችን ዝቅ ብለን ማገልገላችን እንጂ የተቀመጥንበት ቦታ ወይንም ስልጣን እንዳልሆነ ምን ያህል ትረዳለህ? ጌታ ኢየሱስ ዝቅ ብሎ የተከታዮቹን እግር ካጠበ ከእኛስ ምን ይጠበቃል?
9. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

***ማጠቃለያ***

ጌታችን አልፎ በሚሰጥባት በዚያ ሌሊት ከፊቱ የነበረው ፈተና ግዙፍ ቢሆንም ለብዙ ጊዜ ሲመኝ የነበረውንና ታላቅ ፍቅሩን የገለጠበትን የመጨረሻ ዕራት ከደቀመዛሙርቱ ጋር አብሮ ሲበላ እንመለከታለን። በአይሁድ ስርዐት የተዘጋጀውን እንጀራና ወይን በፊታቸው እያሳለፈ ለዓለም መዳን የሚከፈለው ቅዱስ ስጋውና የደሙ ምሳሌ እንደሆነ አስረዳቸው። በዚህም ሳያበቃ ለእነርሱ ያለውን ጥልቅ ፍቅሩን ለመግለፅ በመታጠቢያ ውሃና ማበሻ ጨርቅን ይዞ የሚከደውን ይሁዳን ጨምሮ የሁሉንም እግር ዝቅ ብሎ አጠበ። የጌታ የኢየሱስ ፍቅር እጅግ ታላቅ ነው!! ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውምና። ዮሐ 15:13

**የቃል ጥናት**
"ስጋዬን የሚበላና ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ" ዮሐ 9:16

# ጥናት 53

## ኢየሱስ በጌቴሴማኒ

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 22:39-53

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ጌታ ኢየሱስ ከመከራው በፊት የመጨረሻውን ዕራት ሲበላ እንዲሁም ለእነርሱ ያለውን ፍቅር ዝቅ ብሎ እግራቸውን በማጠብ እንደገለፀ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት አልፎ ሊሰጥበት ወዳለው የአትክልት ስፍራ ሄዶ በአባቱ ፊት ሲፀልይ እናያለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ከእራት በኋላ ኢየሱስ የሄደበት ስፍራ የት ነበር? በዚህ ስፍራ ሲገኝ የመጀመሪያው ይመስልሃል? ጌተሰማኒ የቃሉ ትርጉም ምንድን ነው?
2. የሰው ልጅ ታሪክ የጀመረውና የመጀመሪያው አዳም ኃጢአት በሰራበት በኤደን ገነት የአትክልት ቦታ (ዘፍ 2:7-25 ፤ 3) እና ሁሉተኛው አዳም ለእግዚአብሔ አብ በመታዘዝ የመከራን ጽዋ የተቀበለበትን የጌተሰማኒን የአትክልት ስፍራ በማነፃር ተወያዩበት።
3. ኢየሱስ ከቁ. 40-46 በፍርሃት እያጣጣረ አጽንቶ ይፀልይ ነበር።
   ሀ. ለደቀመዛሙርቱ ምን ብሎ አዘዛቸው?
   ለ. የኢየሱስ ፀሎት ምንድን ነበር? ጽዋው ምንድን ነው?
   ሐ. ደቀመዛሙርቱ በዚህ የጭንቅና የፈተና ወቅት ተኝተው ሲያገኛቸው ምን አላቸው?
   መ. በቁ. 43-44 የኢየሱስ ጭንቀትና መከራው የተገለጸው እንዴት ነው? ይህስ ስለመከራው ክብደት ምን ያሳየናል?
   ሰ. በቁ. 43 ላይ “ከሰማይ መጥቶ የሚያበረታው መልዐክ ታየው” ሲል በመከራ ውስጥ ስለሚያበረታው የእግዚአብሔር ፀጋ ምን ትረዳለህ?

4. ቁ. 47-53 ኢየሱስ ልይዙት የመጡት በምን ዓይነት ሁኔታ ነበር? ለምን? ጴጥሮስ ምን ዓይነት እርምጃ ወሰደ? ኢየሱስ የሆነውን አይቶ ምን አደረገ?
5. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

6. ጌታችን ነገሮች በከበዱበት በዚያ ሌሊት ያደረገው መፀለይና ከአባቱ ጋር ህብረት ማድረግ ነበር? የእኛስ ምን ይሆን?
7. በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ ታምነን ቢመችም ባይመችም ፈቃዱን መፀለይ እንዳለብህ ምን ያህል ታስተውላለህ።

### *ማጠቃለያ*

የሰው ልጅ ታሪክ የጀመረው በኤደን ገነት የአትክልት ቦታ ነው፣ ሐጢአትም እንዲሁ (ዘፍ 2:7-25 ፤ 3)። አንድ ቀንም የሕይወት ዛፍ ያሉባትን አዲሲቷን እየሩሳሌምን እንደተሰፋ ቃሉ እንወርሳለን። በዛሬው ጥናት ጌታ ኢየሱስ በደብረ ዘይት በሚገኘው በጌተሰማኒ የአትክልት ስፍራ የመከራን ጽዋ መቀበሉ አጋጣሚ ሳይሆን እኛን ከኃጢአት የተነሳ ከተወሰደብን የኤደን ገነት ኑሮ የተሻለውን የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ኑሮ ሊያወርሰን ነው። በፈተና ውስጥ እንዳንወድቅ በፀሎት እየተጋን አዲሲቷን ኢየሩሳሌምን እንደ ተሰፋ ቃሉ ልንጠብቅ ይገባናል።

**የቃል ጥናት**
“. . . ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ” ሉቃ 22:42

# ጥናት 54

## ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደ

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 22፡54-65

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ጌታ ኢየሱስ በብዙ ጣር በጌተሰማኒ እንደፀለየና በይሁዳ አልፎ እንደተሰጠ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ደቀመዛሙርቱ ሁሉም ጥለውት ሲሸሹ በተለይም እነዚህ ሁሉ ቢከዱህም እኔ አልለይህም ያለው ጴጥሮስ እንደማያውቀው ሆኖ ሶስት ጊዜ ሲክደው እናያለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. በክፍሉ ኢየሱስ በካህናት አለቆችና በመቅደስ አዛገሮች ተይዞ ሊከሰስ በአይሁድ ሸንጎ ሲቀርብ እናያለን።
   ሀ. ኢየሱስን ይዘው የወሰዱት ወዴት ነበር?
   ለ. በዮሐ 18:15-16 ኢየሱስን በዚህ ወቅት የተከተሉት ደቀ መዛሙርት እነማን ነበሩ?
   ሐ. ሌሎች ደቀ መዛሙርት የት ነበሩ? መሪያቸው በተያዘበት በዚህ አስጨናቂ ወቅት አብረውት አለመሆናቸው ከምን የተነሳ ይመስልሃል?

2. ጴጥሮስ ኢየሱስን ይከተልበት የነበረበት ርቀት ምን ያህል እንደነበረ አስረዳ? ይህ ጴጥሮስ ስለነበረበት ሁኔታና አቋም ምን ያሳየናል?

3. በዚያች ሌሊት ጴጥሮስ እሳት ሲሞቅ አብሮአቸው የተቀመጠው ከእነማን ጋር ነበር? በዚያ በመገኘቱ ምን ዓይነት ፈተና አጋጠመው? ሰዎች ጴጥሮስ የኢየሱስ ተከታይ መሆኑን እንዴት ሊያውቁ ቻሉ? ጴጥሮስ በሦስቱ ጊዜዎች ስለሰጠው መልስ ተወያዩበት።

4. ከሦስቱ ክህደት በኋላ ኢየሱስ በታላቅ ስቃይ ውስጥ ቢሆንም እንኳን ግድ ብሎት ወደ ጴጥሮስ መመልከቱ ምን ያሳይሃል? የጴጥሮስ ምላሽ ምን ነበር?

5. ከቁ. 63 -65 ያለውን ክፍልና ሐዋሪያው ጴጥሮስ በ 1ኛ ጴጥ 2:21-23 የፃፈውን በማነፃፀር ጌታ ኢየሱስ እንዴት ባለ መልኩ እራሱ አሳልፎ እንደሰጠ በዝርዝር ተወያዩበት።

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

6. ጴጥሮስ የጌታ ቃል ትዝ ብሎት ወደ ንስሀ መጣ። አንተስ በኑሮህ ጌታን በማያስከብር ነገር ውስጥ ስትመላለስ ቃሉ ራስህን እንድታይና እንድትመለስ ምን ያህል እየረዳህ ነው?
7. ኢየሱስን ይዘው ሲወስዱት ጴጥሮስም ርቆ ይከተለው ነበር? ዛሬስ ጌታን በርቀት መከተል ጉዳቱ ምንድን ነው? ተወያዩበት።
8. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

እያንዳንዳችን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ በክርስትና ሕይወታችን ስንፍገመገም እንታያለን። ሰይጣን ውድቀታችንንና መሞታችንን ሊያፋጥን በፈተና ላይ ፈተና ቢያመጣም ራሱን አሳልፎ የሰጥን ጌታ ግን እምነታችን እንዳይጠፋ ስለ እኛ እየማለደ "እንደ ዶሮ" ባለ ታዐምራዊ ድምፅ በንስሃ ዳግም ወደ እርሱ እንድንመለስ ያደርገናል። ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን። በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤ እንሰደባለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም፤ የኢየሱስ ሕይወት በሰጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁል ጊዜ የኢየሱስን መሞት በሰጋችን ተሸክመን እንዞራለን። 2ቆሮ 4:7-10

**የቃል ጥናት**
"አንተ ግን እስከ ፍፃሜው ድረስ ሂድ፤ አንተም ታርፋለህ፤ በቀኑም መጨረሻ በዕጣ ክፍልህ ትቆማለህ" ዳን 12:13

# ጥናት 55

# ጲላጦስና ሄሮድስ

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 22፡66-71፤ 23:1-25

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ኢየሱስን ሁሉም እንደሸሹትና ወደ ካህናት ግቢ ተወስዶ እየተዘበተበት የሐሰት ምስክር ፈልገው የሞት ፍርድ እንዲፈረድበት ሲማከሩ ተመልክተናል። ኢየሱስ በመስቀል እንዲሰቀል ከመፈረዱ በፊት ለስድስት የተለያዩ ጊዜውች ተከሶ ለፍርድ ቆሟል። ይህም ለሶስት ጊዜት በአይሁዳዊያን ሸንጎ ሲሆን በተቀሩት በሶስቱ ጊዜያት ደግሞ በሮማዊያን ሸንጎ ነበር። በዘመኑ የአይሁድ ችሎት የሞትን ፍርድ መፍረድ ስለማይችሉ ኢየሱስን ወደ ሮም ሲልኩት እንመለከታለን። በዛሬው ጥናት ይህንን ፍርድ ሊፈርድላቸው ወደሚችለው ወደ ሮም ገዢ ፊት በመረጃ ሲያቀርቡት እናያለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ም. 22:66 ኢየሱስን በቀደምትነት ለክስ ያቀረቡት እነማን ነበሩ? ይህን ያደረጉበት ምክንያት ለምን ይመስልሃል?

2. በም. 22:67-71 ኢየሱስን በአይሁድ ሸንጎ አቁመውት የሚከሱበትን የሀሰት ማስረጃ በመፈለግ ሲጠይቁት ኢየሱስ ስለራሱ ምን ተናገረ? ማቴ 26:64
3. የአይሁድ ሀይማኖት መሪዎች እንደፈለጉት እራሳቸው ኢየሱስን መግደል ያልቻሉበት ምክንያት ምንድ ነው? በም.23:1-7 በጲላጦስ ፊት ያቀረቡት ሦስት ዋና ክሶች ምንድን ናቸው?
4. ጲላጦስ ማን ነው? በቁ. 23:4 መሠረት የመጀመሪያው የጲላጦስ የፍርድ ውሳኔ ምንድን ነበር? ወደ ሄሮድስ ሊልከው የፈለገበት ምክንያት ምን ነበር?
5. እስካሁን ባጠናናቸው ጥናቶች መሠረት ሄሮድስ ማን ነው? ኢየሱስን ሲያይ የተደሰተበት ምክንያት ለምን ነበር? ኢየሱስን በመጨረሻ ለምን ናቀው?
6. በሄሮድስና በጲላጦስ መካከል የነበረ ወዳጅነት ምን ይመስል ነበር? ኢየሱስ በሀሰት ተከሶ በመሀከላቸው መግባቱ ምንን ፈጠረ?
7. ኢየሱስ ሁለት ጊዜ በጲላጦስ ፊት፣ አንድ ጊዜ በሄሮድስ ፊት ለፍርድ ቢቀርብም በሦስቱም ጊዜውች "አንዳ በደል ስንኳ" አላገኙበትም። ጲላጦስ በመጨረሻ "ስቀለው፣ ስቀለው . . ." እያሉ ለሚጮኹት አይሁድ ፈቃድ ለምን አሳልፎ ሰጠው? ለመናቸው እንዲሆን ከፈረደ በኋላ በፊታቸው እጁን ታጥቦ ከደሙ ነጻ ነኝ ማለቱስ (ማቴ 27:24) ምንን ያሳያል?

8. በርባን እንዴት ዓይነት ሰው ነበር? (ዮሐ 18:40 ፤ ሉቃ 23:19) በርሱ ፈንታ ኢየሱስ መሰቀሉን ስታስብ ምንን ያስታውሰሃል?

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

9. ኢየሱስ በጲላጦስ፣ በሄሮድስ፣ በሃይማኖት መሪዎች ጥፋት ሳይገኝበት ይህን ሁሉ ቅጣት መቀበሉ ለአንተ መሆኑ ትረዳለህ? (ኢሳ 53:5)
10. በእኛና በበርባን መካከል ያለው ተመሳሳይነት ምንድ ነው?

### *ማጠቃለያ*

ኢየሱስ የበደላችንን ዋጋ ተቀበለ። ተጨነቀ ተሰቃየም አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። እርሱ የኃጢያታችንን ዋጋ በመክፈሉ እኛ ነፃነትን አገኘን።

**የቃል ጥናት**
"እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደህንነታችን ተግሳፅ በእርሱ ላይ ነበር፤ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን"
ኢሳ 53:5

# ጥናት 56

## የኢየሱስ ስቅለትና መሞት

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 23፡26-49

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ጌታ ኢየሱስ ለሮም ገዢዎች አልፎ እንደተሰጠና እንደተፈረደበት ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለትና ሞት እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ቁ. 26-30 ክርስቶስ ኢየሱስን ሊሰቅሉት ሲወስዱት እያለቀሱ የሚከተሉት የኢየሩሳሌም ሴቶች ምን ትንቢታዊ ንግግር ተናገራቸው?

2. ቁ. 31 "እንግዲ በእርጥብ እንጨት እንዲህ ካደረጉ በደረቅ ምን ያደርጉ ይሆን" ብሎ ሲናገር ምን ማለቱ እንደሆነ አብራራ።

3. ቁ 35-38 "ሌሎቹን አዳንክ . . . ክርስቶስ ከሆንክ እስቲ ራስህን አድን" እያሉ ሲዘብቱበት ኢየሱስ ስለምን መልስ አልሰጠም? ኢሳ 53:7 ፤ 1ጴጥ 2:23-24 በመመልከት ተወያዩበት።

4. ከቁ. 39-43 ከኢየሱስ ጋር ከተሰቀሉት አንዱ ኢየሱስ በተዐምራት ከስቅላት እንዲያድነው በመፈለጉ የተነሳ በሌላኛው ወንጀለኛ ይገሰፀው ነበር። ዛሬ በራሳችን ሀሳብና ፍላጎት ተጉዘን ለሚያጋጥመን ፈተናና ችግር ሀላፊነት እንወስዳለን ወይስ እግዚአብሔርን እናማርራለን? ከነዚህ ከተሰቀሉት አንዱ በአስራ አንደኛው ሰዐት መዳንን የማግኘቱ ምስጥር ምንድን ነው?

5. ቁ. 44-46 በኢየሱስ ህልፈተ ሕይወት የመጨረሻዋ ሰዓት በቤተመቅደስ ውስጥ በቅድስተ ቅዱሳንና በቅድስት መካከል ያለው መጋረጃ መቀደዱ ምን መንፈሳዊ መልዕክት እንዳለው ግልፅ። (ዕብ 9:1-10 ፤ ዕብ 10:19-22)

6. ከቁ 47-49 የሮማ ወታደር የሆነው የመቶ አለቃ "ይህ ሰው በእርግጥ ፃድቅ ሰው (የእግዚአብሔር ልጅ - ማቴ 27:51-54) ነበር ብሎ እንዲል ያሰኘው ምክንያቶች ምንድን ናቸው? በስፍራው የተሰበሰቡት ሰዎች ያደረጉትንስ እንዴት ትረዳዋለህ?

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

7. የቀሬናውን ስምዕንን ግድ ብለው መስቀል እንደተሸከመ ሁሉ በክርስትና የሕይወት ጉዞአችን ከሐጢአት ጋር ሳናመቻምች ዋጋ በመክፈል መስቀል ለመሸከም ምን ያህል ዝግጁዎች ነን? ማቴ 10:37-39 በመልከት ተወያዩበት።
8. እጆቹና እግሮቹ በምስማር ተቸንክረው በመስቀል ተሰቅሎ እያለ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" እያለ ግፍ ለሚያደርጉበት ሲፀልይ ስትመለከት ለሕይወትህ ምን ትምህርት ይቀርልሃል።
9. ከዛሬው ጥናት ምን የተለየ ነገር ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

በምህረቱ ባለፀጋ የሆነው እግዚአብሔር አባታችን ለእኛ ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሳ በበደላችን የሞት ባለዕዳ ሆነን ሳለ አንድያ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለ እኛ አሳልፎ ሰጠ። እርሱ ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ደዌያችንን ተቀበለ ህመማችንን ተሸከመ። በአፉ ተንኮል ሳይገኝበት ለእኛ እንደወንጀለኛ ተቆጥረ። ተገረፈ። የእሾህ አክሊል ደፍተው ዘበቱበት፤ ተፉበት። የሞት ዕዳችንን ለመክፈል ስለእኛ ያውም በመስቀል ሞት ሞተልን። እኛን ሊያፀድቅ እርሱ የደህንነታችን ተግሳፅ ተቀበለ። ጠፊተን የነበርነውን እኛን የራሱ ለማደረግ የተከፈለው ዋጋ እጅግ ታላቅና የከበረ ነው። ስለዚህም በዋጋ ተገዝተናል፤ የራሳችን አይደለንም።

**የቃል ጥናት**
"አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ሉቃ 23:34

# ጥናት 57

## የኢየሱስ መቀበርና ትንሳኤ

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 23፡50-56፤ 24:1-12

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ጌታ የኢየሱስን ስቅለትና መሞት ተመልክተናል። በዛሬ ጥናት ደግሞ ስለ ቀብሩና ትንሳኤው እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. የአርማቲያሱ ዮሴፍ ማን ነው? ስለ እርሱ የተፃፈ ምን ነገር አለ? በጲላጦስ ፊት ሄዶ የኢየሱስን አስከሬን መጠየቁና በሚገባ መገነዙ እንዲሁም ማንም ባልተቀበረበት ከአለት በተወቀረ መቃብር አስከሬኑን ማሰረፉ ስታይ ከዚህ ሰው ተግባር ምን ዓይነት ሕይወት እንዳለው ትረዳለህ?

2. ከሳምንቱ መጀመሪያ መግደላዊት ማሪያም፣ ዮሐና፣ የያዕቆብም እናት ማርያምና ከእነርሱም ጋር የነበሩት ሴቶች ወደ መቃብሩ ሲሄዱ ምን ሆኖ አገኙ? የታተመውን ድንጋዩ ማን ያንከባልልናል ያሉትን ተንከባሎ ሲያዩት ምን ዓይነት ስሜት የተሰማቸው ይመስልሃል?

3. ማልደው ወደ መቃብሩ ስፍራ ለሄዱ ሴቶች መላዕክት የነገራቸው ምንድ ነው? ኢየሱስ ህያው ስለመሆኑ በክፍሉ የተገለፁትን በማብራራት ተወያዩበት።

4. ሐዋሪያት ከጌታ ጋር በነበሩ ጊዜ ደጋግሞ የነገራቸውን የትንሳኤ ጉዳይ ከመቃብር የተመለሱ እህቶች ሲነግሯቸው ስለምን መቀበል ያቃታቸው ይመስልሃል? ጴጥሮስ ወደ መቃብሩ ቦታ ሮጦ መሄዱስ በምን ምክንያት ነው ትላለህ? ከዚህ ምን እንማራለን።

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

5. ከቁ. 50-54 የአይሁድ ሸንጎ አባል ከሆነው ዮሴፍ ህይወት በኃጢአተኞች ሸንጎ በፅድቅ መኖር እንደሚቻል ምን ያህል ተማርክ? በኑሮአችን ከዚህች ዓለም ነውርና ዕድፍ ተጠብቀን እንዴት መመላለስ እንደምንችል ተወያዩበት።
6. እግዚአብሔር አብ የሞትን ጣር አስወግዶ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሞት ያስነሳው ለእኛ ለምናምን ከሁሉ በላይ ታላቅ የሆነውን ኃይሉን አውቀን ትንሳኤውን በሚመስል ትንሳኤ እንደምንካፈለው እንድናውቅ መሆኑን ከኤፌ 1:19 እና ሮሜ 6:4-5 በመነሳት ተወያዩበት።
7. እምነታችንም ሆነ ስብከታችን ከንቱ እንዳይሆን ኢየሱስ ከሙታን በትንሳኤ መነሳቱ ብቻ ሳይሆን እርሱ ራሱ የትንሳኤ ጌታ መሆኑን የሚያስረግጥልን ምንድን ነው ትላለህ? ዮሐ 11:25

### *ማጠቃለያ*

ኢየሱስ ተነስቷል!!! እግዚአብሔር አብ ከሁሉ በላይ ታላቅ በሆነው ኃይሉና አሰራሩ የሞትን ጣር አስወግዶ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን አስነሳው። እርሱም በሲኦል እንደማይቀር፣ ስጋውም መበስበስን እንደማያዩ አስቀድሞ በነብያት የተጻፈው ተፈጸመ። የሞት መውጊያ ተሰበረ። ሞት ተሸነፈ። በትንሳኤው ጉልበት ጠላት ድል ተነሳ። በትንሳኤው ለምናምን በርሱ የዘላለም ሕይወት አገኘን። ህያው የሆነው ጌታችን በመንፈሱ ሟች ለሆነው ሰውነታችን ህይወትን ይሰጣልና። በትንሳኤው ኃይል ክፉ የሆነውን የስጋችንን ስራ ገድለን እንደ እግዚአብሔር ልጆች በመንፈስ እየተመላለስን ትንሳኤውን እናውጃለን።

**የቃል ጥናት**
"ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጉታላችሁ፤ ተነስቷል እንጂ በዚህ የለም" ሉቃ 24:5

# ጥናት 58

## የኤማሁስ መንገደኞች

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 24፡13-49

### *መግቢያ*

ባለፈው ጥናት ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ትንሳኤ ተመልክተናል። በዛሬው ጥናታችን ከደቀ መዛሙርቱ መሀከል ተስፋ ቆርጠው ስለሆነው ነገር እያወሩ ኤማሁስ ወደሚባል መንደር ሲጓዙ የትንሳኤው ጌታ በመካካላቸው ተገኝቶ አብሮአቸው ሲጓዝና ሲያወራቸው እንመለከታለን።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ኤማሁስ ወደሚባለው መንደር ሲሄዱ የነበሩት ሁለት ደቀመዛሙርት ሲነጋገሩ የነበሩት ዋነኛው ነገር ምንድን ነበር? ኢየሱስም ቀርቦ ሶስተኛ ሰው ሆኖ አብሯቸው ሲሄድ ምን አላቸው? በጊዜው ኢየሱስ መሆኑን ያላወቁበት ምክንያት ምንድን ነው? ተወያዩበት።
2. እነዚህ መንገደኞች በመንገድ ላይ እያወሩ በ"ነበር" ሲናገሩ የነበሯቸው ነገሮች ምን ነበሩ? ይህ ስለነበሩበት ሕይወትና አቋም ምን ያሳያል።
3. ኢየሱስ ተስፋ ቆርጠው ለነበሩት ለነዚህ ሁለት ጓደኛሞች በጊዜው እየሆነ ስላለው ነገር ለማስረዳት የተጠቀመው ምን ነበር? መልዕክቱስ ምን ነበር? መልዕክቱ በልባቸው ምን ዓይነት ሁኔታን ፈጠረ?
4. ወደሚሄዱበት መንደር በቀረቡ ጊዜ ለኢየሱስ ያቀረቡለት ጥያቄ ምንድን ነበር? ኢየሱስም ወደቤታቸው መግባቱ፣ በማዕድም አብሮ መቀመጡ የደከሙትን ለመመለስ ያለውን የጌታን ፍቅር ምን ያህል ታስተውላለህ? ተወያዩበት።
5. እነዚህ ሰዎች አብሮአቸው የነበረው እንግዳ ኢየሱስ መሆኑን ያወቁት መቼ ነበር? ባወቁ ጊዜ ምን እርምጃ ወሰዱ?

### *የማዛመድ ጥያቄዎች*

6. በክርስትና ሕይወታችን ስንደክም ወይንም ተስፋ ስንቆርጥ በሕይወታችን የሚታዩ ነገሮችን በመዘርዘር ተወያዩበት።
7. ዛሬ በሕይወታችን ተስፋ የሚያስቆርጥን (ያደከመን) ነገር ምንድ ነው? ከዛሬው ጥናት ለተስፋ መቁረጥ (ለመንፈሳዊ ሕይወት ድከመት) የሚሆን መፍትሔ ምን ተማርክ?

### *ማጠቃለያ*

እግዚአብሔር ዛሬም የዳግመኛ አምላክ ነው። የደካማውን መጥፋት ከቶ አይወድም። ከወደቅንበት አዘቅት (ቦታ) ሊያወጣን ዛሬም የፍቅሩ እጅ አላጠረችም። የኤማሁስ መንገደኞች ወደ ቤታቸው አስገብተውት በማዕድ እንደተቀመጡ ዛሬም ፈቅደው ወደ ሕይወታቸው ለሚጋብዙት ሁሉ ሊገለጥላቸው፤ ሊያበረታቸው፤ ተስፋቸውን ዳግም ሊያለመልም ይችላል።

**የቃል ጥናት**

"እየጠወለጋችሁ ስትሄዱ፤ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሯቸ እነዚህ ነገሮች ምንድር ናቸው?" ሉቃ 24፡17

# ጥናት 59

## የኢየሱስ ሕያውነትና ዕርገት

**የምንባብ ክፍል፡** ሉቃ 24:36-54

### መግቢያ

ባለፈው ጥናት በእምነት ዝለው ወደ ኤማሁስ መንደር ሲጐዙ ስለነበሩት ደቀመዛሙርት ተመልክተናል። በዛሬው ጥናት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያውነትና ዕርገት እንመለከታለን።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ በተዘጋ ቤት ውስጥ ገብቶ "ሰላም ለእናንተ ይሁን" ሲላቸው በደቀመዛሙርቱ ውስጥ ምን ዓይነት ስሜት ተፈጠረ? ኢየሱስ በሕያውነት ለእነሱ ከመገለጡ በፊት በምን ዓይነት ስሜት ውስጥ የነበሩ ይመስልሃል?
2. ኢየሱስ ሕያውነቱን ያረጋገጠላቸው መንገዶች ምንድን ነበሩ? ተወያዩበት።
3. ኢየሱስ በቁ. 38 "እናንትም ለዚህ ምስክሮቼ ናችሁ" ብሎ የትንሳኤው ምስክሮች እንደሆኑ ሲነግራቸው ይህን ትልቅ ኃላፊነት የሚወጡበትን ሊሰጣቸው የገባላቸው ቃል ምንድን ነበር? ለዚህም የሰጣቸው መመሪያ ምን ነበር?
4. ኢየሱስ በቁ. 50 ላይ ወዴት ወሰዳቸው? ከዕርገቱ በፊት በመጨረሻ ምን አረገላቸው?
5. በመጨረሻም ኢየሱስ እያዩት "ወደ ሰማይ አረገ"። ደመናም ከዐይናቸው ሰውራ እስክትቀበለው ደቀ መዛሙርቱ ምን ያደርጉ ነበር? ከዚያስ በኋላ ምን አደረጉ?

### የማዛመድ ጥያቄዎች

6. የክርስቶስ ትንሳኤና ሕያውነት ምስክር ለመሆንና ይህን ኃላፊነት ለመወጣት የመንፈስ ቅዱስን አስፈላጊነት ምን ያህል እንደሆነ ትረዳለህ?
7. ሕያው የሆነው ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እያዩት እንዳረገ፤ አንድ ቀን በክብር ሲገለጥ ዓይኖቻችን እንደሚያዩት ስታስብ ምን ይሰማሃል።

### ማጠቃለያ

ከዘመናት በፊት በነብያት እንደተነገረው የሰው ልጅ ስለ ኃጢአት አሳልፎ ተሰጠ፤ ተሰቀለ፤ በሶስተኛውም ቀን በትንቢት ፍፃሜ በትንሳኤ ተነሳ። ይህም ጌታ ለሐዋሪያትና ሲከተሉት ለነበሩት ቅዱሳን በተለያዩ ቦታዎች ተገለፀ። አንዳንዶችም የተወጉ እጆቹን አይተው ህያው እንደሆነ አወቁ። የገሊላ ሰዎች በክብር ሲያርግ እንዳዩት አንድ ቀን ዳግም ይመለሳል። አስወድሞ ግን ለሕዝቦች ሁሉ የንስሃና የሐጢአት ስርየት ይሆን ዘንድ የመንግስቱ ወንጌል በእኛ ይሰበካል። "ሰላም ለእናተ ይሁን" እንዳለ እኛም የእርሱን ሰላም እስከ ምድር ዳርቻ እናውጃለን። ኢየሱስ ይመጣል!!

### የቃል ጥናት

"የገሊላ ሰዎች ሆይ፤ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁ እንዲሁ ይመጣል" ሉቃ 18:27